# መንፈሳዊ ምግብ በትክክለኛው ጊዜ

እመን ብቻ፡ እመን ብቻ፣
ሁሉ ይቻላል፡ እመን ብቻ

አሁንስ እንዴት፡ እንዲህ ነው፤

አሁን አምናለሁ፣ አሁን አምናለሁ፣
ሁሉም ይቻላል፡ አሁን አምኛለሁ፡
አሁን አምናለሁ፣ አሁን አምናለሁ፣
ሁሉም ይቻላል፡ አሁን አምኛለሁ።

እንደ ቆምን፡ ራሶቻችንን ዝቅ አድርገን እንቆያለን።

ጌታ ሆይ፡ ይህ “አሁን አምናለሁ!” መዝሙር፡ መዝሙር ብቻ ሳይሆን፡ የልባችንም ጥልቅ ዝማሬ ይሁን፡ አንድ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ፡ ኢየሱስ ብዙ ተአምራትን ካደረገ በኋላ፡ “ጌታ ሆይ፡ አሁን እናምናለን፡” አሉት።

ኢየሱስም “አሁን ታምናላችሁን? ” አላቸው፤

2 “ሁሉንም ነገር እንደምታውቅ ማንም እንዲያስተምርህ እንደማያስፈልግ እናምናለን፡” አሉት። አባት ሆይ፡ ዛሬ ማታ ዕውቀታችን እንደማያስፈልግህ፡ እኛን ግን የአንተ እንደሚያስፈልገን እውቀናል። ስለዚህ እንዴት እንድንጸልይ፡ እንዴት እንድንኖር፡ እና እንዴት እንድናምን እንድታስተምረን እንጸልያለን። ጌታ ሆይ፡ በዛሬው ምሽት አገልግሎት፡ ይህን ስጠን። ጌታ ሆይ፡ አንዳች ቢጎድለን፡ ስጠን። በኢየሱስ ስም ጸለይን። አሜን።

3 ብዙዎቻችሁ ዛሬ ማታም እንደቆማችሁ አውቄአለሁ። እንዲሁም ውጪ፡ መግባት አልቻልንም ያሉ ወገኖችን አግኝተናል፡ በተለያዩ መኪኖች ውስጥ ሆነው በሬዲዮ እያዳመጡ ነው። ስለሆነም ዛሬ ማታ በተቻለን መጠን ፈጠን ፈጠን ለማድረግ እንሞክራለን፡ የእሁድ ምሽቱን ብዙውን ሰአት ለታመሙ ሰዎች ለመጸለይ የምናውለው ይሆናል፡ ልክ እንደገባን የጸሎት ሰልፍ ይኖረናል። የዛሬ ምሽት አገልግሎት ግን ለታመሙት ለመጸለይ እንጠቀምበታለን።

4 ስለዚህ አሁን… በእግዚአብሔር ቅዱስ ቃላት ዘንድ፡ በእምነቱ ዘንድ፡ በዚህ ዘመን እምነት፡ እንድትገነቡ እፈልጋችኋለሁ። ይህ እምነት! ዘመኑ በየትኛውም ዘመን ከነበረው የበለጠ እምነት የሚጠይቅ ነው፡ ምክንያቱም፡ የመነጠቅ እና የመወሰድ እምነት ነው። ስለዚህ ዛሬ ምሽት ያያችሁትን፡ እና የሰማችሁትን፡ ሲሰበክ የሰማችሁት ቃል ሁሉ፡ ምልክቶች፡ ሲደረጉ——ያያችኋቸው ድንቆች እንድታምኑ እንፈልጋለን። ይህ ሁሉ በአንድነት በልባችሁ እንድታከማቹ እና፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነ እና እንዳለሆነ፡ እንድትመዝኑት እንፈልጋለን።

5 ኤልሳዕ በብሉይ ኪዳን፡ “እግዚአብሔር እርሱ አምላክ ከሆነ፡ እርሱን አገልግሉት፡” ብሏል። ኢየሱስም ለክርስትና የሁሉም ነገር ማዕከል ከሆነ፡

እንግዲያውስ ሁሉንም ነገር ትተን ወደ እሱ መጣበቅ ያለብን ይመስለኛል። እስታውሱ፡ እርሱ ማዕከል ነው፡ የስሜኑ ኮከብ እርሱ ነው፡ መደምደሚያው እርሱ ነው፡ ፍጹም እርሱ ነው። የሰሜን ኮከብ እርሱ ከሆነ... ወደ ሰሜን ኮከብ የሚጠቁም አንድ አለ፡ እርሱም አብራችሁ የምትጓዙት ኮምፓሳችሁ ነው። እናንተም እንድትጓዙበት የምፈልገው ኮምፓስ ቃል ነው፡ ቃል ሁሌ ወደ እርሱ ይጠቁማል።

6 እንግዲህ ታላቅ የጭንቀት እና የፈተና ጊዜ ውስጥ እንዳለን ይሰማኛል፡ የጊዜ ግራ መጋባት እና በህዝቦች መካከል ያለው አለመረጋጋት፡ እና ሁሉም ዓይነት ነገሮች እየተከሰቱ ይገኛሉ፡ አንዳንድ ጊዜ ተጠራርጎ እንደተወሰደ፡ ባየሁት ቦታ ሁሉ፡ በባህር ላይ እንደ... ሚወዛወዝ መርከብ ይሆንብኛል። እንዴት እናደርገዋለን? የመርከቡን ሀላፊነት ለእኔ ተሰጥቶኛል። ከመርከቤ መቶ እጥፍ የሚበልጥ፡ ነጭ ራስ ያለው እነሆ መጣ። እኛ ግን ሁሉንም፡ እንነግራቸዋለን። "በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለንና።" ካፒቴኑ፡ ዋናው ካፒቴን፡ በመርከቧ ጫፍ ላይ ያለውን ልጓም ይይዛል፡ ይጎትተዋል። እያንዳንዳችንን እንነግራቸዋለን።

7 አሁን፡ ዛሬ ማታ፡ ፈጠን እንበልና በጊዜ እንለቃችኋለን... ከርቀት እሽከርክራችሁ መምጣታችሁ፡ እና እንዴት እያሽከረከራችሁ እንደምትሄዱ፡ እና የምትከፍሉትን መስዋዕት ወዘተ ሁሉ፡ እጅግ እናደንቃለን። ይህም፡ እያችሁ፡ እናንተን ለማገዝ የምችለውን ያህል እያደረግኩና እየተናገርኩ መቆም ባለብኝ ጸንቼ እንድቆም ያደርገኛል። እዚህ በምሆንበት ጊዜ ሁሉ ግን፡ እዚሁ ላለንባት ወቅታዊ ሁኔታ ማገዝ እንድችል የተቻለኝን ሁሉ ለማድረግ እተጋለሁ። እናንተም ትወስዳላችሁ... መቼም በእንዴ ለሰዎች ስትዘረግፋላቸው ማስታወስ አይችሉም። አንዲት ነገር ለአንድ ሰው ከሰጣችሁ በኋላ ነገሩን ማየት እስኪችሉ ድረስ—ያዝ ማድረግ አለባችሁ። ነገሩን በልባቸው ጠንከር አድርገው ከያዙ በኋላ፡ እራሳቸው ስለሚፈልጉት... ሌላ ነገር አስተምሯቸው። አካሄዳችን ልክ ደረጃ በደረጃ ነው።

8 አሁን፡ ጸልዩ እና አይዟችሁ በርቱ፡ ለዛሬው ማታ ፈውስ ተማመኑ። አሁን ስለምንኖርበት ጊዜ በውስጣችሁ ጥያቄ ያለ አይመስለኝም። እግዚአብሔር በህዝቡ መካከል ነው ወይስ አይደለም የሚለው በውስጣችሁ ጥያቄ አለ ብዬ አላምንም። ሁላችሁም እንደምታምኑ አምናለሁ። እኔም... በአዕምሮዬ ምንም ጥርጣሬ የለብኝም። ህዝቤ የሆኑት፡ ወዳጆቼ፡ የክርስቶስ ወዳጆች፡ የክርስቶስ—ልጆች የሆኑቱ፡ ይሄን እንደሚያምኑ እው—እው—እውቃለሁ።

9 ከእግዚአብሔር ዘንድ መልዕክት መቀበላችሁን እውቃችሁ፡ ለህዝቡ መስጠት መቻላችሁን ስትገነዘቡ ህዝቡም ራሱ ደግሞ መልስ ሲሰጥበት ማየት፡ እጅግ ደስታን ይፈጥርባችኋል። ከዚያም ወደ ኋላ መለስ ብላችሁ "አባት ሆይ፡ አመሰግናለሁ፡" ትላላችሁ። አቤቱ፡ ልጆች የተላከላቸውን እንጀራ ሲበሉ ማየት ምንኛ የሚያስደስት ነው! ከዓመታት በፊት እዚህ ቤተ ክርስትያን ውስጥ በራእይ ደረጃ የነበረ እንደሆነ አስተውላችኋል? ትክክል ነው፡ "የህይወት እንጀራ።" ወንድም ኔቪል፡ ታስታውሰዋለህ። ልዩና—ታላቅ ጊዜ!

10 ንባቡን ለመከተል ወይም ማስታወሻ መያዝ ከፈለጋችሁ፡ አሁን ሁላችንም የምናነበው... የፈውስ አገልግሎትም ይሁን ሌላው ዓይነት ላይ፡

የእግዚአብሔርን ቃል ሳያነቡ እና ጥቂት አስተያየቶችን ሳይሰጡ፡ ጉባኤ ማድረጉ ተገቢ ነው ብዬ አላምንም። ሁላችንም እናውቀዋለን። በመካከላችን፡ እንግዳ ያለ አይመስለኝም። ፈውስ ምን እንደሆነ ግን ሁላችንም እናውቃለን። የሆነ ግለሰብ የሚያደርግላችሁ አይደለም፡ እግዚአብሔር አስቀድሞ ለእናንተ ያደረገው ነገር ነው። መዳንም ያው ነው። ብቸኛው ነገር፡ ህዝቡ፡ ያ እውነት መሆኑን እንዲያምን ማድረግ ነው። እግዚአብሔር እራሱ በቃሉ በኩል ያስተምራል ከዚያም ላመኑት ሁሉ ማረጋገጫ ያደርግላቸዋል፡ እንዲህ ብሏልና፦ “ለሚያምን ሁሉ ይቻላል።”

11 እናንተም “ለእግዚአብሄር የሚሳነው ነገር የለም፡” ትላላችሁ። እንዲህ እንደሆነ ታምናላችሁን? እንግዲያውስ፡ ለእናንተም የሚሳናችሁ ነገር የለም። “**ለሚያምኑ** ሁሉ ይቻላቸዋልና፡” (እግዚአብሄር አንድ ነው) “ለሚያምኑ ነው።” አያችሁ? እናንተም፡ እመኑ ብቻ እንጂ፡ የሚሳናችሁ ነገር የለም።

12 አሁን ከአንደኛ ነገሥት፡ ምዕራፍ 17፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ የመጀመሪያዎቹን ሰባት ቁጥሮች አነባለሁ።

> **በገለዓድ ቴሰቢ፡ የነበረው ቴሰብያዊው ኤልያስ፡ አክዓብን፡ በፊቱ የቆምሁት፡ የእስራኤል አምላክ ሕያው እግዚአብሔርን፡ ከአፌ ቃል በቀር፡ በእነዚህ ዓመታት ጠልና ዝናብ አይሆንም አለው።**
>
> **የእግዚአብሔርም ቃል እንዲህ ሲል፡ ለእርሱ መጣለት፡**
>
> **ከዚህ ተነሥተህ፡ ወደ** ምሥራቅ **ሂድ፡ ወደ ምሥራቅ ሂድ፡ በዮርዳኖስም ትይዩ ባለው በኮራት ፈፋ ውስጥ ተሸሸግ።**
>
> **እንዲህም ይሆናል፡** ከወንዙም **ትጠጣለህ፡ ቊራዎችም በዚያ ይመግቡህ ዘንድ አዝዣለሁ።**

አስተውሉ፡ “**በዚያ** ይመግቡህ ዘንድ፡” በሌላ ቦታ ሳይሆን። “በዚያ!”

> **ሄደም ጌታ** እንዳለውም **አደረገ፡** ወይም **እንደ ጌታ ቃል አደረገ፡ ሄዶም በዮርዳኖስ ትይዩ ባለው፡ በኮራት ፈፋ ውስጥ ተቀመጠ።**
>
> **ቊራዎቹም በየጠዋቱ እንጀራና ሥጋ ያመጡለት ነበር፡ በየማታውም እንጀራ እና ሰጋ ያመጡለት ነበር፡ ከወንዙም ይጠጣ ነበር።**
>
> **ከብዙ ቀንም በኋላ፡ በምድር ላይ ዝናብ አልነበረምና፡ ወንዙ ደረቀ።**

13 ጌታ በቃሉ መነበብ ላይ በረከት ይጨምር። አሁንም፡ ለዛሬ ማታ፡ “መንፈሳዊ ምግብ በትክክለኛው ጊዜ፡” የሚል ርዕስ፡ ከዚህ መውሰድ እፈልጋለሁ። ዛሬ ጠዋት በነበረን—በትምህርታችን—ላይ “እግዚአብሔርን ማገልገል መሞከር፡ ወይም ጊዜው፣ ወቅቱ፣ ቦታው፣ ወይም ሰውዬው ሳይሆን… ያለ እርሱ ፈቃድ እርሱን ለማገልገል መፈለግ ነበር።” አሁን ደግሞ፡ **መንፈሳዊ ምግብ በትክክለኛው ጊዜ።**

14 ይህ ኤልያስ፡ የተባለው ነብይ፡ ስለ እርሱ የምናውቀው በጣም ጥቂት ነው። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ባርያ እንደነበረ፡ ለዚያች ዘመን እርሱ የእግዚአብሔር ባርያ እንደነበረ እናውቃለን።

15 እግዚአብሔር፡ በኤልያስ ላይ የነበረውን መንፈሱን፡ ሦስት ጊዜ ተጠቅሞበታል፡ በተጨማሪ ሁለት ጊዜ፡ ባጠቃላይ አምስት ጊዜ፡ ለጸጋ እንደሚጠቀምበት ቃል ገብቷል። በኤልያስ ላይ ተጠቅሞበታል፡ በኤልሳዕ ላይ እጥፍ ድርብ ሆኖ መጣ፡ በመጥምቁ ዮሐንስ ላይ ነበር፡ አሁንም የአህዛብ ሙሽሪት ለማውጣት ሊመጣ ይገባል፡ አይሁድን ወደ ቤት ለመውሰድ ከሙሴ ጋር ደግሞ ይመጣል። ትክክል ነው። እግዚአብሔር የኤልያስን መንፈስ አምስት ጊዜ እንደሚጠቀምበት ቃል ገብቷል፡ እስከ አሁን ሦስት ጊዜ ሰርቶበታል።

16 አሁን፡ ይህ ታላቅ ነብዩ፡ ከየት እንደመጣ አናውቅም። ቴስቢታዊ መሆኑ ብቻ እናውቃለን። እንዴት እንደመጣ ግን...

17 ስለ ነብያት የምናውቀው ነገር ጥቂት ነው። ከወዴት እንደመጡ አናውቅም። አልፎ አልፎ... እንደው፡ እኔ ከቤተክርስትያን ይውጡ ወይስ ከበሰተጀርባቸው የዘርሐረግ ይኑራቸው አንዳች አላውቅም። ብቻ ፍርሐት የሌለባቸው፡ እና፡ ብዙ ጊዜ፡ ያልተማሩ ተራ ወንዶች ናቸው። እንዲሁም እራሳቸው የጻፋት ጽሑፍ፡ የላቸውም። ኢሳይያስና ኤርምያስ፡ ሁለቱ፡ አንዳንድ ጽሑፎችን ጽፈዋል፡ ኤልያስ የተባለው ይህ ታላቅ ሰው ግን አንድም ነገር ጽፎ አያውቅም። ብዙዎቹ አልጻፉም፡ ምናልባት መጻፍ አይችሉም ነበርና፡ ነገር ግን ቆራጥ ሰዎች ነበሩ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ እነዚያ የጥንት ነቢያት ያለ ማንም ሰው የለም። መንግሥታትን፣ ነገሥታትን፣ ሕዝቦችን፣ ቤተ ክርስቲያንንና ሌሎችን ሁሉ እየተቃወሙ፣ በእግዚአብሔር ቃል ጸንተው ቆሙ፡ እግዚአብሔርም ትክክል መሆናቸውን መሰከረላቸው። በጣም ቆራጥ ግለሰቦች ነበሩ።

18 ይህ ኤልያስም ከሁሉም ይልቅ እጅግ የቆረጠ ሰው ነበር። እርሱም የምድረ በዳ ሰው ነበር። በምድረ በዳ ይኖር ነበርና፡ ከምድረ በዳ ወጥቶ መጣ። መጽሀፍ ቅዱስ ጸጉራም ነገር ለብሶ ነበር ይለዋል። በወገቡ ላይም የግመል ቁርበት፡ ትንሽ ቆዳ እና፡ የበግ ለምድም ይለብስ ነበር፡ ፊቱም... እጅግ ጢማም ነበረ፡ እኔ እንደሚመስለኝ ሰውዬው ለማየት የማይመች-ወጣ ገባ-መልክ የነበረው ይመስለኛል።

19 እኛ ግን... ሁሉም ግን አልሞቱም። ሁሉም––ሁሉም አልሞቱም። በኒቂያው ጉባኤ ዘመን፡ **የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ኒቂያ ጉባኤን** ያነበባችሁ ሰዎች፡ ሌሎች አብያተ ክርስትያናት ሁሉ ሰባብረው ወደ አንድ ለመምጣት በፈለጉ ጊዜ፡ ድርጅት ለመመስረት በፈለጉ ጊዜ፡ የኒቂያ ጉባኤ ባደረጉ ጊዜ፡ እንደ ኤልሳዕ የመሳሰሉ፡ ቅጠላ ቅጠል ብቻ የሚመገቡ፡ ታላላቅ እና ቆራጥ ሰዎች ከምድረ በዳ መጡ። ባለ ሥልጣናቱ ግን፡ በቆስጠንጢኖስ ሥር የነበሩ፡ ከፍተኛ ባለ-ሥልጣናት፡ ወዘተረፈ ግን፡ ድምጻቸውን አፈኑ። ምክንያቱ እነዚያ፡ ነቢያት በመሆናቸው፡ በሙሽራው ውስጥ የነበረው የሰንዴ ቅንጣት መሬት ውስጥ መውደቅ እንደነበረበት ሁሉ፡ የሙሽራዋ ቤተ ክርስትያን የሰንዴ ቅንጣት መሬት ላይ መውደቅ እንዳለባት አውቀው ነበርና። ለአንድ ሺ አመት በዚያ መተኛት ነበረባትና።

20 ለዚህም ነው ዛሬ በመጽሃፍቱ ውስጥ፡- "ቆሞ የሚያይ ዝም ያለው አምላክ የት አለ፡ ሕፃናትን ሲገደሉ፡ ሴቶችም በአንበሶች ሲቀደዱ፡ በሰማይም ተቀምጦ ስለ እርሱ ምንም አይናገርምን ይላሉ? " ቃሉን ስለማያውቁት ነው። የሰንዴ ቅንጣት መሬት ላይ መውደቅ አለባትና። ጻድቅ የሆነው አምላክ የራሱን ልጅ

ሲሞት እና ሲተፋበት፡ ወዘተ እንዴት ቆሞ ይመለከታል? ግን በቃሉ መሰረት ነው፡ መፈጸምም ነበረበትና። እስከዚህ ሰዓት ድረስም እንደዚህ ነውና።

21 ይህ ሰው፡ ታላቅ ሰው ነበር። በፊቱ የነበረው ትውልድ ኃጢአተኛ ነበረ። አክዓብም ነግሶ ነበር፡ ከእርሱ በፊት የነበረ አባቱ ክፉ ሰው ነበር። ከሰለሞን በኋላ፡ አንዱ ከሌላው እየቀጠሉ ክፉዎች ነበሩ። በሰማርያ ሀያ ሁለት ዓመት የነገሠው ይህ አክዓብም፡ ከሌሎች ሁሉ ይልቅ የከፋ ነበረ። የተለየ ዘመናዊ ሰው ነበር። አለጥርጥር፡ በሐይማኖት የሚያምን ሰው ነው። በዘመናዊ አደራረግ ሁሉም አይነት ነገር ነበረው። የራሱ የሆኑ አራት መቶ ዕብራውያን ነቢያት ነበሩት፤ ሁሉም በደንብ-የተማሩና የሰለጠኑ ነበሩ። እግዚአብሔር ግን አንድ ሰው ላከበት እርሱም ኤልያስን ነበረ፡ እሱ ግን አላመነበትም።

22 ይህ ቴሰብያዊ ኤልያሰ ግን የምድረ በዳ ሰው ነበረ። ቆራጥ ሰው ነበር እንጂ፡ ለሰላሳ ሰው አልነበረም። አንድ ቀንም አክዓብ በሰራው ኃጢአት እግዚአብሔር መቋቋም ሰላልቻለ፡ ኤልያሰን በምድረ በዳ ተናገረው። እሱም እዚህ በተደጋጋሚ እንደተናገርኩት፡ እነሆ ወደ ሰማርያ መንገድ ወረደ፡ ምናልባት ነጭ ጢሙ ፊቱ ላይ ተጣብቋል፣ ራሰ በረሀው ፀሐይ ላይ ያበራል፣ አይኖቹም ያረጁ ጠባብ ናቸው፡ በእጁ ዱላ ይዟል፡ በፊቱም ፈገጋታ፡ ወደ እሰራኤል ንጉሰ ወርዶ፡ ተናገረ፦ “እልሃለሁ... ከአፌ ቃል በቀር ጠል እንኳን አይወርድም።”

23 እግዚአብሔር እንደነዚህ ያሉትን ሰዎች ይሰጠን፡ እያችሁ፡ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ሲሉ የሚያደርጉትን የሚያውቁ ሰዎች ይሰጠን።

24 እንግዲህ፡ ይህን ከማድረጉ በፊት፡ እግዚአብሔር እንደጠራው ተረድተናል። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ተነጋግሮ ነበርና፡ በዚህም ምክንያት፡ ምንም ነገር አልፈራም። መልዕክቴ አይፈጸምም ብሎ፡ አልፈራም፡ እንደሚፈጸም አውቆ ነበርና! እንደ ጌታ ቃል እንደሆነና፡ እሱ ራሱ የዘመኑ የእግዚአብሔር ነቢይ መሆኑን አውቋልና። ሰለዚህ ንጉሡ ራሱን ቢቆርጠው፡ ወደ እሰር ቤት ቢወረውረው፡ ምንም ቢያደርጉት፡ ለሱ ለውጥ የለውም፡ በንጉሱ ፊት ለፊት፦ **“የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡”** የሚልበት ተልዕኮ ነበረው። እንዴት ያለ ቆራጥ ሰው ነው! ይህን ከማድረጉ በፊት ግን፡ ታላቅ ድርቅ ይሆናል አለ...

25 እግዚአብሔር ኃጢአትን ያለ ቅጣት አይተወውምና። ቅጣት መኖር አለበት። ቅጣት አልባ ህግ—ምን ይጠቅማል? “መብራት ጥሶ ማለፍ ህግ መጣሰ ነው፡” ከተባለ፡ ከበሰተጀርባው ግን፡ ምንም አይነት ቅጣት ወይም መቀጮ ከሌለው፡ ለምን ይጠቅማል? ህግ ሊሆን አይችልም። ሰለዚህ ለኃጢአትም ቅጣት አለው። እግዚአብሔር ህግ ሲያወጣም ያ ህግ—ህጉ ከተጣሰ፡ ለዚያ ቅጣት ሊኖር ይገባል።

26 ይህች አገርም ህጉን ሁሉ ጥሳለች። ኦህ፡ ትልቅ ቸርች ነበራቸው፡ መቅደሰም ነበራቸው። ብዙ የተማሩ ሰዎች ነበሯቸው። በመላው አገሪቱ ነቢያት ነበሯቸው፡ ትምህርት ቤቶች ነበሯቸው፡ እንደ ማሽን ይፈለፍሏቸው ነበር። ብዙ ነቢያት ነበሯቸው፡ ብዙ—ካህናት ነበሯቸው፡ ብዙ ጸሐፍትም ነበሯቸው፡ ብዙ ሃይማኖቶች ነበራቸው፡ ከእግዚአብሔር ቃል ግን የራቁ ነበሩ። ሰለዚህ እግዚአብሔርም በነዚህ ሁሉ ሹመቶች በመካከላቸው የሌለ አንድ ሰው ጠራና፡ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ከሚል ቃል ጋር ላከው።

27 እንደው ስለወገኖቹ እንዴት እንደሚያስብ ተመልከቱ። ይህን ነብይ መልዕክትን አስይዞ ከመላኩ በፊት፡ እንዲህ አለው፡- "ኤልያስ፡ ወደ ንጉሱ ወደ አክዓብ ውረድና እነዚህ ነገሮች ተናገር አለው። ከዚያም፡ ከተናገርከውምም በኋላ፡ ከሱ ዘንድ ፈጥነህ ሽሽ፡ በድርቁ ዘመን አንተ የምትሸሸግበት ስፍራ እኔ አዘጋጅቼልሃለሁ። ኤልያስ ሆይ፡ ቃሌን ብቻ ብትሰብክ፣ አድርግ ያልኩህን ብቻ ብታደርግ፣ እኔ እንከባከብሃለሁ።"

28 አሁን ዛሬ ምሽት፡ ይህ ታላቅ የኤልያስ አገልግሎት፡ እና የኤልያስ ዘመን በጥላ እያመሳሰልኩ፡ አሁን እየኖርንበት ካለው ዘመን ጋር አመሳስለዋለሁ። ፍጹም የሆነ ምስሌው ነውና። እንደው... መለሰ ለማለት... ጊዜ ካገኘን፡ ስለ ህዝቦች አስባለሁና፡ ይሁን እንጂ ለጸሎት ሰልፍ በዛ ያለ ጊዜ መውሰድ እፈልጋለሁ።

29 ስለዚህ ወደ ኋላ መለስ ብለን ስናይ፡ እስራኤል ፍልስጤምን የያዘችበት መንገድ እኛ ይህች ዩናይትድ ስቴትስን በያዝንበት ተመሳሳይ መንገድ ነው። ወደ ዩናይትድ ስቴትስ መጥተን፡ ይኖሩባት የነበሩ ህንዳውያንን በማባረር፡ ምድሪቱን ወረስናት። እስራኤልም በእግዚአብሔር ሥር፡ በኢያሱ መሪነት፡ ወደ ፍልስጤም ገብተው፡ ሰፍረውባት የነበሩትን በማባረር ምድሪቷን ወረሱ።

30 የመጀመሪያዎቹ ነገሥታቶቻቸውም ኃያላን ሰዎች እነ ዳዊት፣ ሰሎሞን ታላላቅ ሰዎች ነበሩ። የመጀመሪያዎቹ ፕሬዚዳንቶቻችንም፡ እነ ዋሽንግተን፣ እነ ሊንከን፣ እና የመሳሰሉት ታላላቅ ሰዎች ነበሩ። ከዚያም በመጨረሻ ፕሬዚዳንቶቹ ወይም ነገስታቶች በጊዜው ብዛት እየበሰሉ ይሄዳሉ፣ በመጨረሻ ፍጻሜአቸውም እንደ አክዓብ ይሆናል። ትክክለኛ ምሳሌ፡ የዘመናችን ምሳሌ። ህዝቡም ሁሉ እጅግ ዘመናዊ ስለሆኑ እውነተኛው የጌታን ቃል መሰማትን አልፈለጉም።

31 እውነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋይ፡ እንደነዚህ ባሉ ዘመናዊ ሰዎች ፊት፡ ምን ሊመስላቸው እንደሚችል መገመት ትችላላችሁ። "በፊታቸው፡ እብድ ሆነባቸው፡ አእምሮው ለቋል። እንዲህ ያለ ነገር ሊኖር አይችልም።" እነርሱም ሐይማኖተኞች፡ እጅግ ሐይማኖተኞች ናቸው። በመካከላቸውም ብዙ ልባም ሰዎች፡ ልባም ህዝብ ነበራቸው። እጅግ ሐይማኖተኞች ነበሩ።

32 ስለዚህ ይህ ነገር ከተራ ስነ መለኮት ይልቅ የተሻለ ነገር እንደሚጠይቅ፡ ከተራ መልዕክት ይልቅ—የበለጠ እንደሚፈልግ፡ ጠጣር ልባቸውን ለመስበር፡ ቃሉን ከመሰበክ ይልቅ ከፍ ያለ ነገር እንደሚፈልግ ያውቃል። በዛ ህዝብ ላይ ፍርዱን ለማውረድ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር እንዲህ ይላል** የሚል ቃል እንደሚያስፈልግ ያውቃል። የሰራዊት ጌታ እግዚአብሐር እንዲህ ይላል የሚል ቃል ይዞ ከወጣ (**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዳለው** እንደሚሆን ያውቃል።)፣ ያንን መቃወም፡ ፍርድ ነበር። በዘመናችንም፡ አይተነዋልና። በሁሉም ዘመናት አይተነዋል። የምህረትን መስመር ስታልፉ ከፍርድ በቀር የሚቀር ነገር አይኖርም።

33 አሁን፡ ያ ምሳሌ፡ ያን፡ ኤልያስን ከዛሬ ቤተ ክርስቲያን ጋር፡ ከዛሬዋ ቤተ ክርስትያን ጋር እመሰለዋለሁ። እርሱ ይህን መልእክት፡ ከፍርድ በፊት ተቀበለ። እንደ እግዚአብሔር ቃል፡ ለሶስት አመት ከስድስት ወር፡ ወይም፡ ኤልያስ እኪናገር ድረስ፡ ዝናብ ስለማይዘንብ፡ ኤልያስ ለስጋው የሚሆን ምግብ

ማግኘቱ፡ በስጋ እንክብካቤ ሲደረግለት፡ ምሳሌአዊ ነበር። “ኤልያስ፡ አንተ ይሁን ባልከው ሰዓት፡ እርሱ ይሆናል።” ስለዚህም ወደ ንጉስ ወርዶ፡ እንዲህ አለ፦ “ቃል ከአፌ እከማወጣ ቀን ድረስ ጠል እንኳን አይወርድም።” እንደው ከበድ ያለ—ነገር ነው፡ አይደል? የተለየ መልዕክት ነው!

34 አሁን ደግሞ ይህ ነገር ዛሬ ካለው መንፈሳዊ ድርቅ ጋር እናመሳስለዋለን። በመንፈሳዊ አነጋገር፡ ዛሬ፡ በምድሪቱ ላይ፡ ታላቅ መንፈሳዊ ድርቅ እንዳለ፡ ሁላችንም እናውቃለን። በነብያት ሁሉ በትንቢት እንደተነገረ፡ የነገሩ ፍጻሜ፡ ክርስቶስ ዳግም ከመምጣቱ በፊት እንደሚሆን፡ ታውቃላችሁን? “በምድር ላይ ራብ ይመጣል፡ ራቡም የእግዚአብሔር ቃል ለመስማት እንጂ፡ ስለ እንጀራ ብቻ አይሆንም፡” ብለዋል። “እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል የሚሰማበት፡” ያ ጊዜ አሁን ነው። አሁን፡ የተፈጥሮ ድርቅ የመንፈሳዊው ምሳሌ ነው።

35 በሐሰተኞች እና በዘመናዊ አስተማሪዎች፡ ቤተክርስትያን ውስጥ የገባ ሐጥያት እና አለማመን፡ ሰፍራውን ወደ እንዲህ አይነት ሁኔታ፡ ወደሚመጣ ፍርድ አድርሶታል። ከእግዚአብሔር ቃል እና የእርሱ ከሚሆን ነብይ፡ ወደ ዘመናዊ ሰነ መለኮታዊ የቃል ፍቺ ዞር ብለዋል።

36 እዚህ ላይ ካስተዋላችሁ፡ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ አንድ ነገር የሚያነሳው በዚያን ዓይነት ጊዜ ነው። ምክንያቱ፡ እርሱ፡ ሁልጊዜ፡ አስቀድሞ ለሰዎች ሳይገልጥ ምንም አያደርግም፣ የሚገልጠውም ሁልጊዜ በባርያዎቹ ነው።

37 አሁን፡ ኤልያስ ግን፡ በዚህ ጊዜ፡ እግዚአብሔር እንዲሄድበት የወሰነለት ሚስጥራዊ ቦታ ነበረው። የጸሎት ሰልፍ ከመጥራታችን በፊት አሁን ማየት የምንፈልገው ያ ነው። ኤልያስ በራሱ በእግዚአብሔር የተዘጋጀለት ሚስጥራዊ ቦታ ነበረው። ቤተ ክርስቲያን አላዘጋጀችለትም፣ ንጉሱም አላዘጋጀለትም፣ ራሱም ለራሱ አላዘጋጀም፣ እግዚአብሔር ግን ለኤልያስ በድርቁ ዘመን ሁሉ የሚዘጋጅለትን ምግብ፡ ዕለት ዕለት የሚመገብበት ምስጢራዊ ስፍራ አዘጋጅቶለታል። ነገ ምን ይውጠኛል ወይም ምንጩ ይደርቅብኛል ብሎ መጨነቅ አያስፈልገውም ነበር። እግዚአብሔር “ቁራዎች እንዲመግቡህ አዝዣለሁ እነሱም ይመግቡሃል፡” አለው። እንዴት ያለ ድንቅ ነገር ነው፡ በክርስቶስ ያለን ምስጢራዊ ቦታ ምሳሌ ነው።

38 የዓለም የጉባኤው ምክር ቤት እና ዛሬ እየተካሄደ ያለው ሁሉ፡ “የተአምራት ዘመን አልፏል፡” እያሉን ነው። የእግዚአብሔር ታላላቅ ኃይሎችም ከቤተ ክርስቲያናት ተወስደዋል። ከአሁን በኋላ፡ ምንም ነገር የላቸውም፡ “የሚጮህ ናስ እና የሚንሿሿ ጸናጽል፡” መስሏልና። እውነት መሆኑንም እናውቃለን። “የአምልኮ መልክ አላቸው፡ ኃይሉን ግን ክደውታልና።”

39 እንደ ዛሬው ጠዋት፡ ዳዊት ያደረገው ተመሳሳይ ነገር ነው፡ እርሱ ከበሬ ጋሪዎቹ ጋር፡ ከእግዚአብሔር ቃል ራቀ። ቃሉ ቀርቦ ሲሰጣቸው፡ አልፈለጉትምና፤ ስለዚህም፡ ከእርሱ ፈቀቅ ብለው ራቁ።

40 በኤልያስ ዘመን የነበሩ ሰዎችም ያደረጉት ይህ ነው፡ ከቃል ፈቀቅ ብለው ርቀዋል። ቃሉ ያላቸው ይመስላቸው ነበር፡ ይሁን እንጂ አልነበራቸውም።

41 ስለዚህ አስተውሉ፡ እንግዲህ፡ እርሱ… የማያምኑትን ሊቀጣ በወደደ ጊዜ፡ ለአማኙ መንገድ አዘጋጀለት። ሁሌም የሚያደርገው ያው ነው። አለምን በውሃ ሊያጠፋ በወደደ ጊዜ፡ ለኖህ የማምለጫ መንገድን

አዘጋጀለት። ግብፅን ሊያሰጥም በወደደ ጊዜ፡ ለሕዝቡ የማምለጫ መንገድን በባሕር አደረገላቸው። እንዴት እግዚአብሔር መንገድ እንደሚያወጣ! መንገድ በሌለበትስ እንኳ፡ እርሱ ራሱ መንገድ ነው። እሱ መንገድ ነውና!

42 አሁንም እኛ ታሪክ ከሚያውቃቸው ጊዜዎች ውጪ የሆነ... ለየት ያለ ዘመን እየተጋፈጥን እንዳለን ተገንዝበናል። መፍራት ያለብን፡ የሚያብረቀርቅ የጦር አፈሙዝ ያለው፡ ጭንቅላት የተገጠመለት ሚሳይል አይደለም። ልንፈራቸው የሚገባን አብያተ ክርስቲያናትን ነው። ልንመለከተው የሚገባን የምንኖርበት ዘመን ነው።

43 አሁን አስተውሉ፡ እግዚአብሔር ግን ለኤልያስ የሚያመልጥበትን መንገድ አዘጋጀለት። አሁንም ለሚያምኑት ልጆቹ ከቁጣው እና ከሚመጣው ነገር፡ የሚያመልጡበትን መንገድ አዘጋጅቷል።

44 ምክንያቱ፡ እግዚአብሔር ሶዶምን እና ጎሞራን እንዲሰጥሙ አድርጎ፡ በዚያ የነበሩትን ህዝብ ሁሉ ቀጥቶ፡ ቅፍርናሆምንም በባሕር መካከል አሰጥሞ፡ በዚያ የነበሩትን ሁሉ፡ እና ሶዶም እና ጎሞራን ኰንኖ፡ እኛ እነርሱ ያደረጉትን ሰናደርግ ዝም ካለን ጻዲቅ ሊሆን አይችልም። እነርሱ ፍርድን በርግጥ እንደተቀበሉ እኛም ፍርድን በርግጥ እንቀበላለን። አሁን እናስተውል...

45 እነዚህ ነገሮች፡ በዚያ ዘመን የነብሩ ዘመናዊ አደራረጎች በበቀሉ ጊዜ፡ እግዚአብሔር በዚያ ዘመን ሰው አስነሣ፡ ወይም፡ እነዚያን ኃይላትን የሚዋጋ አንድ ሰውን አስነሣ፡ እነርሱ ግን አልሰሙትም። አብደዋል አሉት፡ አይምሮው የሳተ ሰው መሰላቸው፡ ተራ ወግ አጥባቂ፡ ከምድረ በዳ የወጣ ሞኝ፡ ቁጥቋጦ-ያሳበደው መሰላቸው። የጌታን ቃል፡ ግን፡ በሱ ዘንድ ነበረ።

46 ዛሬ ዛሬ "ቃሉ የሚናገረው እንዲህ ለማለት ፈልጎ አይደለም፡" ይላሉ። "ኡህ፡ ደግሞም፡ኮ፡ መጽሐፍ ቅዱስ የታሪክ መጽሐፍ ነው።" እንደው ይሄን አይታችኋል ብዬ እሰባለሁ፡ አሁን፡ ሲናገሩ፡ "ሄዋን አፕል አልበላችም፡ የበላችው ኧ... " ምን ነበረ? አሁን በላች የሚሉት... "አፕሪኮት ነው፡" መሰለኝ። "አፕሪኮት ነበር።" ሌላው ደግሞ፡ በተጨማሪ፡ "ሙሴ ህዝቡን በቀይ ባህር አላወጣቸውም። በባህሩ በአንደኛው በኩል ማዶ ላይ፡ ብዛት ያለው ትልልቅ የሸንበቆ ዘለላ ስለነበረ፡ በሸንበቆው ባህር ውስጥ አልፎ ሄደ።" ውህው፡ ደብልዩ-ኤ-ቲ-ኢ-አር፡ በሁለቱ ጫፍ እንደ ግድግዳ እንዴት መቆም ቻለ፡ እንዴትስ፡ በደረቅ መሬት ተሻገሩ? ኡህ፡ መቼም ከንቱነት ነው! ይሁን እንጂ፡ እያችሁ፡ በህዝቡ ላይ የእግዚአብሔርን ቁጣ ለማውረድ እንደዚያ ያለ ቀን ይፈለጋል። አዎን።

47 እንዲህ የሚባል ነገር የለም—ይላሉ... የቤተ ክርስትያን ሰዎች ሳይቀር በተአምራቶች አያምኑም። "ተአምር አሳየኝ፡ ተአምር አሳየኝ!" "እኔ አንድ ሺህ ዶላር እሰጥሃለሁ፡" ይላሉ። እንደው፡ አስር ሺ ተአምራቶች በፊታቸው ቢደረግ እንኳን አያዩትም። ለምን፡ በፍጹም፡ ሊያዩት አይችሉምና።

"ይህ አይቻልም፡" ብላችኋል። ኧረ፡ የማይቻል፡ አይደለም።

48 አንድ ጊዜ ኤልያስ ወደ ዶታን ወረደ፤ የሶርያ ሠራዊትም የአገሪቱ ሰልጣን፡ የበላይ ጠባቂ፡ በዚያ እንደሚገኝ አውቀው—ልይዙት መጥተው፡ ከተማይቱን ከበቧት። ንጉሱም፡ ማን ነው ሲል... ከወጣቶቹ አንዱ የሶርያን ንጉስን፡

እንዲህ ብሎት ነበርና፡ “ለምን፡ ታውቃለህ፡ ቴስቢታዊው፡ ነብይ ኤልያስ፡ አንተ በእልፍኝህ ሆነህ የምታወራው ምስጢር ለእስራኤል ንጉስ ስለሚናገር ነው።”

49 እርሱም “እንቅፋት የሆነብን ይህ ሰው! ሄዳችሁ ይህን ሰው ያዙ፡” አላቸው። የሶርያ ሰራዊት በሙሉ በዶታን ዙርያ ሰፈረ። ሁሉም ከበዋት ነበርና።

50 የ—የነብዩው ሎሌ፡ ጊያዝ፡ ማልዶ ነቃና፡ እንዲህ አለ፡ “ኧረ፡ አባቴ ሆይ፡ ሰራዊቱ ሁሉ በዙርያችን ከቦናል። ሙሉ ለሙሉ ተከበናል።”

51 እርሱም “እንዴ፡ ከእነርሱ ጋር ካሉት ከእኛ ጋር ያሉት ይበዛሉ፡” አለው። አያችሁ?

ጊያዝ ግን ዙርያውን አይቶ፡ “ኧረ’ኔስ ምንም አልታየኝም፡” አለ።

52 እርሱም አለ፡ “ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡ የብላቴናውን አይኖች ክፈት።” ዓይኖቹም ተገለጡ፡ ተራራዎቹም ሁሉ በዙሪያው የተቀመጡ መላእክትና ሰረገሎች፡ የማይታዩ ኃይሎች ሞልተው ነበር።

53 ኤልያሰም ወደዚያ ሄደ፡ መጽሐፍ ቅዱሰም እንደሚል፡ “የሁሉም አይኖች አሳወረ።” ወደ እነርሱም ወጣ፡ እርሱን ማየት አልቻሉም፡ ወጥቶም እንዲህ አላቸው፡- “ኤልያሰን እየፈለጋችሁ ነውን? ”

“አዎን፡ እሱን እየፈለግን ነን፡” አሉ።

54 “ኑ፡ እርሱ ያለበትን እኔ አሳያችኋለሁ፡” አላቸው፡ ይዞ ሰራዊቱ ወዳደባበት ሰፍራ መራቸው፡ እነርሱም በቀጥታ ወጥተው ያዟቸው።

55 አሁን፡ መጽሀፍ ቅዱሰ እንደሚል፡ “የሁሉም አይኖች አሳወረ ነው።” አለቀ። ጌታ አምላክ በሕዝቡ መካከል ወርዶ፡ በተሰፋው ቃል የተናገራቸውን ነገሮች ምንም ቢያደርግም፡ ሰዎች ዛሬ መንፈሳዊ ዕውሮች ሆነዋልና፡ በምንም አያዩትም። መንፈሳዊ ዕውሮች ናቸው፡ እግዚአብሔርን አያውቁም፡ ታላቁን ኃይሉን አያውቁትም። አሁን፡ በኤልያሰ ዘመን ያደርጉት እንደነበር፡ አሁንም እንደሚያደርጉት እናሰተውላለን። እግዚአብሔር ዓይኖቻቸውን አሳውሯልና። ዛሬም፡ “ተአምር የሚባል የለም፡ እንደዚህ ያለ ነገር የለም፡ ይህ ሁሉ ሰሜት ነው፡” ይላሉ።

56 ሰለ ኤልያሰ ተመሳሳይ ነገር ያወራሉ፡ ወደ ሰማይ ከተወሰደ በኋላ፡ ወጣቱ ኤልሳዕ የሱን ሰፍራ ተካ፡ ራሰ በረሀ፡ ወጣት ነበር፡ ልጆች ከኋላው እየሮጡ፡ እንዲህ አሉት፡ “አንተ መላጣ፡ ለምን ከኤልያሰ ጋር አልወጣህም? ” አያችሁ፡ ይህ ሁሉ ነገር ከተፈጸመ በኋላ እንኳን፡ ህዝቡ፡ ከመጀመርያም ጀምሮ አላመነበትም። ይህ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው በእሳት ሰረገላ ወደ ሰማያት ተወሰደ፡ ሕዝቡ ግን አሁንም አላመኑም። ህጻናት ልጆቻቸው ከዚህ ሰው ጀርባ እንዲሮጡ አድርገው፡ እንዲህ አሉ፡ “አንተ መላጣ፡ ለምን ወደ ላይ አልወጣህም? ” አያችሁ? ነቢዩም ልጆቹን ረገማቸው፡ አንዲት ድብ ከእነርሱ አርባ-ሁለቱ ልጆች ገደለቻቸው።

57 አሁንም አሰተውሉ። ዛሬም፡ እንደ ድሮ፡ ለቃሉ የራሳቸውን ትርጓሜ አሰቀምጠውበታል። እንግዲህ፡ እነርሱ እንዲህ ማድረጋቸው፡ የራሳቸው ጉዳይ ነው፡ ችግሩ ግን እኛን ለማሳመን ይሞክራሉ። መጽሀፍ ቅዱሰ ሲናገር፡- “የእግዚአብሔር ቃል በግል የሚተረጎም አይደለም።” እግዚአብሔር የራሱ ትርጓሜ ያደርጋል ይላል። እግዚአብሔር ቃሉን ያጸናል፡ ፍቺውም ያው ነው።

ደጋግሜ እንዳልኩት፡ በመጀመሪያ፡ “ብርሃን ይሁን አለ፡” ብርሃንም ሆነ። ያ መተርጎም አያስፈልገውም፡ ተፈጸመ። “ድንግል ትፀንሳለች አለ፡” ጸነሰች። “መንፈሴን አፈሳለሁ” አለ፡ አፈሰሰው። እርሱም፡ “በመጨረሻው ዘመን፣” አደርጋለሁ ያላቸው ነገሮች፡ እያደረጋቸው ነው! እግዚአብሔር የራሱን ትርጓሜ እየሠራ ነውና፡ ምንም ዓይነት ትርጓሜ አያስፈልገውም። ሞኝ ሰው ምንም ቢናገር፡ ቅንጣት ያህል እግዚአብሔርን አያስቆምም።

58 ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ፡ ዛሬ ካለንበት ጋር የሚስተካከል ምናልባትም የበለጠ፡ እርሱ የሚታገለው አለማመን ነበረ። ነገር ግን አላስቆመውም፡ ግዳጁን እየፈፀመ እና እየተወጣ ይሄድ ነበር፡ እግዚአብሔርም ያደረጋቸውን ነገሮች ያረጋግጥለት ነበር። እርሱም ሲናገር፦ “ብቻየን አይደለሁም። እኔና አባቴ አንድ ነን፡ እርሱ በእኔ ውስጥ ይኖራል። ሥራን የምሠራው እኔ አይደለሁም፣ በእኔ የሚኖረው አብ ነው እንጂ። ሥራውንም ባላደርግ፡ አትመኑኝ፡ እኔ ሥራውን ባደርግ እናንተ ግን ባታምኑኝ፡ ሥራውን እመኑ።” አያችሁ? በሌላ አባባል፡ እነርሱን... “መጻሕፍትን ትመረምራላችሁ፡” አላቸው፡ “ቅዱሳት መጻሕፍትን በመመርመር፡ የዘለአለም ህይወት የምታገኙ ይመስላችኋልና። ቅዱሳት መጻሕፍት፡ ግን፡ ስለ እኔ ይመሰክራሉ።” አሜን! እንዴት ያለ ንግግር ነው! “እነርሱም፡ ማለት ቅዱሳት መጻሕፍት፡ ስለኔ ይነግሯቹኋል፡” አለ ኢየሱስ።

59 እኛ ስለምንኖርበት ዘመን የሚነግሯችሁም ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው። ሲደረጉ ያያችኋቸው ነገሮች፡ እግዚአብሔር ራሱ በህዝቡ መካከል ሆኖ የሚያደርጋቸው ናቸው። ከእግዚአብሄር በቀር ሙታን ማስነሳት የሚችል የለም። አሁን የሚያደርጋቸውን ነገሮች ከእርሱ በቀር ማንም ማድረግ አይችልም። መጽሐፍ ቅዱስም “እርሱ ትናንትና፣ ዛሬ፣ እስከ ለዘላለም ድረስ ያው ነው፡” ይላልና።

60 አሁን የሕዝቡን ዘመናዊ አሰራር እናያለን፡ እና፡ “ኦህ፡ ቀኖቹ አልፈዋል፡ ተአምር ብሎ ነገር የለም። ሰዎቹ ሁሉ ስሜት ውስጥ ገብተው ነው።”

61 ያንን ነብዩው፡ ኤልያስ፡ በእነርሱ ላይ እና በሰነ መለኮት ምሁራኖቻቸው ላይ ድምጹን አውጥቶ እንዴት እንደሚገሰጻቸው ሰሙት። እስተውሉ፡ እስተውሉ፡ እርሱ ሲናገር እግዚአብሔር እንደተናገረ ነበረ። ኤልያስ እንደ እግዚአብሔር ተናገረ፡ “እኔ እስክጠራው ድረስ ጠል ከሰማይ አይወርድም።” አሜን! የሰ፡ ሰር።

62 ነቢዩ በእግዚአብሔር ፊት ረጅም ጊዜ ቆይቷል፡ በብሉይ ኪዳን ነቢያት፡ ወይም በማንኛውም ጊዜ፡ ቃል እስኪሆኑ ድረስ በእግዚአብሔር ፊት ሲኖሩ፡ መልእክቶቻቸው ራሱ ቃል ነው። ደግሞም፡ አትርሱ፡ እርሱ ሲናገር **“የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር እንዲህ ይላል፡”** ብሏልና። እናም እነዚያ ሰዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ መልእክቶች ሲቀበሉ፡ ከአሰተሳሰባቸው ውጪ እስኪሆኑ ድረስ... ምናልባትም ከሰተሳሰባቸው ጋር የሚቃረን ሊሆን ይችላል፡ በትክክልም—አልተረዱትም ይሆናሉ። ነገር ግን **“የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር እንዲህ ይላል፡”** የሚል ቃል ይናገሩ ነበር።

63 “እኔ እስክጠራው ድረስ ምንም ዝናብ አይኖርም።” ኦህ፡ እንዴት ያለ ንግግር ነው! በእግዚአብሔር ፊት ስለቆየ ፍጹም በሆነ መልኩ ተረጋግጧል።

እንዲሁም፡ አሞጽ 3:7ን እንደሚደግፈው፡ አስታውሱ፡ "ጌታ እግዚአብሔር አስቀድሞ ለባርያዎቹ ለነቢያት ካልገለጠ በቀር ምንም አያደርግም።" አለም፦ "ምንም ዝናብ አይዘንብም!" እሱ ካላለ...

64 ሳቁበት፡ ያበደ መሰላቸው፡ "ወግ አጥባቂው!" ይሁን እንጂ፡ አያችሁ፡ ዝናብ እንደማይዘንብ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር እንዲህ ይላል** ነበረው። እግዚአብሔርም፡ ይህን ከማድረጉ በፊት፡ ለባሪያው ለኤልያስ፡ ገለጠው። እሱም የተረጋገጠ፡ ምስክር ያለው ነቢይ ነበር፣ ስለዚህ ህዝቡም ንሰሃ መግባት ነበረበት። ይሁን እንጂ፡ በዚያ ፈንታ፡ ሳቁበት፡ እንዲህም አሉ፦ "ኧረ፡ ዝናብ'ማ በዝቶልናል! ግድቦቻችን ሞልተዋል። ወንዞችም ሞልተው ይፈሳሉ።"

65 መጽሐፍ ቅዱሰም፡ "ለሦስት ዓመት ከስድስት ወር ጤዛ እንኳን አልነበረም።" ይላል። ጅረቶች ሁሉ እና ውሃዎች በየቦታው ደርቀው ነበር። እግዚአብሔር በዚያ ሰው አልፎ ስለተናገረ እንጂ፡ ከሰውዬው አልነበረም። "እኔ" የሆነው እርሱ ራሱ ነበር። ሁሌም እናውቀዋለንና። ስለዚህ ሰው...

66 በእግዚአብሄር ተቀብቶ፡ **የሰራዊ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡** ከሚል እውነት ጋር፡ ከእግዚአብሔር የተላከ ሰው ሰናገኝ፡ መልእክቱ እና መልእክተኛው አንድ እና አንድ ናቸው። ምክንያቱ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር እንዲህ ይላልን፡** ቃል በቃል የወከለ ስለሆነ፡ እሱ እና መልእክቱ አንድ ናቸው።

67 በሐይማኖት ተቋም መንፈሳዊ ስራ የሚሰራ፡ የሐይማኖት ተቋም ሰው፡ እሱ እና ቤተ ክርስትያኒቱ "አንድ" ናቸው። በአንድ የሐይማኖት ተቋም ያደገ፡ በሥነ መለኮት ሥር ያለ የሥነ መለኮት ምሁር፡ እሱና መልእክቱ አንድ ናቸው፤ በሰነ መለኮት ቤተክርስትያን፡ የሰነ መለኮት ምሁር ነው። በትክክል።

68 ከዚያም ግን አንድ ሰው **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ጋር ሲመጣ፡ እሱና መልእክቱ አንድ ናቸው። ስለዚህ ኤልያስ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል እያለ በመጣ ጊዜ፡ እሱና መልእክቱ አንድ ሆኑ። ልክ እንደ ኢየሱስ፡ እሱ ሲመጣ፡ ዮሃንስ 1 ላይ፡ ቃል እንደነበረ። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል እና የዘመኑ መልእክተኛ ሁል ጊዜ፡ አንድ አካል ናቸው። ትክክል ነው።

69 ኢየሱስ በትንቢት የተነገረ ቃል ነበር። "ድንግል ትጸንሳለች ይህ ወንድ ልጅ ትወልዳለች፡" በማለት ነብያት ይሆናል ብለው የተናገሩት ነበረ። ድሮ በመጀመርያ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ በማለት ነገራቸው፦ "የሴቲቱ ዘር የእባቡን ራስ ይቀጠቅጣል፡ እርሱም ሰኮናዋን ይቀጠቅጣል።" እነዚህ ሁሉ ትንቢቶች ተሰጥተው ነበር። ዳዊትም እና፡ በዘመናት ሁሉ የነበሩት ነቢያት ሁሉ፡ ስለ እርሱ ተናግሯል። የተከሰተው ቃል እርሱ ነበር! ሃሌሉያ!

70 አሁን ምን መዳሰሰ እንደፈለግኩ አያችሁ? ዛሬ ማለዳ ከእናንተ ጋር በግልጽ ተናገርኩት። የሕያው የእግዚአብሔር ሰልጣን፡ ሕያው በሆነች ቤተ ክርስትያን፡ በሙሽራይቱ ዘንድ አይታያችሁምን? ድውያን ይፈወሳሉ፣ ሙታን ይነሣሉ፣ አንካሶች ይሄዳሉ፣ ዕውሮች ያያሉ፣ ወንጌል በኃይሉ ችሎት ይሰበካል፡ መልእክተኛው እና መልእክቱ አንድ ናቸውና። ቃሉ በቤተ ክርትያን ዘንድ፡ በሰውዬው ዘንድ ነው።

71 የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ጋር በወጣ ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል በኤልያስ ውስጥ ነበረ፡ እርሱም፦ “ዝናብ አይዘንብም” አለ። እግዚአብሔር በኤልያስ ነበረ እንጂ፡ ኤልያስ አልነበረም።

72 አንድ ጊዜ የክርስቲያን ሳይንስ እመቤት ያለችኝን፡ ብዙ ጊዜ ተናግሬአለሁ። ይህ ጉዳይ ብዙ ጊዜ ተናግሬዋለሁ። “አቶ፤ ብራንሃም፡ ብዙ ጊዜ ስለ ኢየሱስ ታካብዳለህ፡” አለችኝ።

“መልስ መስጠት ያለብኝ ለዚያ ብቻ ነው ብዬ ተሰፋ አደርጋለሁ፡” አልኳት።

አክላም “መለኮታዊ ልታደርገው ትሞክራለህ፡” አለችኝ።

አዎን “መለኰት ነበር፡” አልኳት።

73 “ኦህ፡ እሱ መልካም ሰው ነበር፡ ነብይ ነበረ እንጂ፡ መለኮታዊ አልነበረም፡” አለችኝ።

74 እኔም “እሺ፡ እንዳልነበረ የሚገልጽ አንድ ቃል አሳዬኝ፡” አልኳት።

75 እሷም “በዮሃንስ ወንጌል ላይ፡ ወደ አልዓዛር መቃብር በወረደ ጊዜ ‘አነባ’ ይላል፡” አለችኝ።

76 “እሺ፡” አልኳት፡ “አዎን፡ አነባ። ሰው እና መለኮት ሁለቱ ነበረ። እንደ ሰው፡ አለቀሰ፡ ሙት ለማስነሣት ግን አምላክ መሆን ነበረበት።” በትክክል። “እንደ ሰው፡ ተርቦ ነበር፡ በአምስት አሳ እና በሁለት እንጀራ፡ አምስት ሺ የመገበ አምላክ ግን ነበር፡” አልኳት። ልክ ነው። “በጀልባ ጀርባ ላይ፡ እንደ ሰው ተኝቷል፡ በውስጡ ግን ውቃውን ጸጥ የሚያደርግ እግዚአብሔር ነበረ።” ለምን? እሱና መልእክቱ አንድ ናቸው።

77 “እኔና አባቴ አንድ ነን። አባቴ በእኔ ይኖራል፡” ብሏል። የመለኮት ሙላት በአካል እርሱ ነበር።

78 በቀደም **ሰባቱን የቤተክርስቲያን ዘመናት** ሳስተዋውቅ፡ በጣም የሚያስደንቅ የነበረ ይመስለኛል። ለመጀመር ያክል፡ ከእነዚያ... በራሱ ላይ ከነበረ ከነጭ ነገር ጋር——ኢየሱስ ነው ለማለት ተቸግሬ ነበር፡ “ጸጉሩም እንደ ባዘቶ ነጭ ነበረ፡” ይላል። ስለዚህ የሰላሣ-ሦስት ዓመት ወጣት ሲሆን እንዴት እንደበረዶ የነጣ ጸጉር ሊኖረው ቻለ አልገባኝም።

79 ውድ ጓደኛዬ፡ የጴንጤቆስጤ ሰነ መለኮት ምሁር፣ ጥሩ ጓደኛ ጋር ደወልኩለት። እና፡ ጃክ ሞር ነው። ብልህ እና፡ አስተዋይ ሰው ነው። እሱም “ወንድም ብራንሃም፡ ይህ’ኮ ኢየሱስ ከከበረ በኋላ ነው። ከከበረ በኋላ እርሱ እንዲህ ይመስላል፡” አለኝ። አይ፡ ይሄን ማመን አልችልም። አይደለም።

“እሺ፡ ወንድም ሞር፡ አመሰግናለሁ፡” እ——እ——አልኩት።

80 ክፍል ውስጥ ገብቼ ከእግዚአብሔር ጋር መናገር ጀመርኩ። በዳንኤል መጽሐፍ ውስጥ፡ ማጣቀሻውን ከፈትኩትና እንዲህ ይላል፡ “ጸጉሩም ነጭ ወደሆነው በዘመናት ወደ ሸመገለው መጣ ይላል።” “ጌታ ሆይ፡ ምን ማለት እንዳለብኝ እ——እ——አላውቅም፡ ደግሞም እኔ ሐላፊነት አለብኝ፡” አልኩት። እንግዲህ አስታውሱ፡ ይሄ ማለት፡ ገና-... ሰባቱ ማሕተሞች ሳይከፈቱ፡ ከአንድ

አመት ወይም ከዚያ በላይ፡ በፊት ነው። “ጌታ ሆይ፡ ይሄ ምንድነው? ” ብዬ እየጸልይኩ ነበር፤

81 እኔም አየሁ፡ እነሆ በፊቴ ቆሞ አየሁት፡ የቆመውም ሰው ዳኛ ነበር፡ በራሱም ላይ ነጭ ዊግ ነበረ። የጥንት ዳኞች ሉአላዊ ሥልጣን እናዳላቸው ለማሳየት ነጭ ዊግ ያጠልቁ ነበር።

82 ከዚያም ኢየሱስን ከነጩ ዊግ ጋር ባየሁት ጊዜ፦ ሉአላዊ ባለስልጣን መሆኑን የምናውቀውን እውነት ብቻ፡ የሚያረጋግጥ ነው አልኩኝ። እግዚአብሔርም በደብረዘይት ተራራ ላይ ተመሳሳይ ነገር መሠከረ፡ እንዲህም አለ፦ “ሉአላዊው ባለስልጣን፡ የምወደው ልጄ ይህ ነው፡ እርሱን ስሙት!”

83 ከዚያም በሰባቱ ማኅተሞች መጀመሪያ ላይ፡ እነዚያ ሰባት መላእክት በዚያ ፒራሚድ ሲወርዱ፡ እዚያ ቆሞ ወደዚህ ተመልሼ በሰባቱ ማኅተሞች ላይ እንድናገር፡ እርሱም ከእኔ ጋር እንደሚሆን፡ ጠፍተው የነበሩ ነገሮች፡ ምን እና ምን እንደነበሩና፡ አሳይሃለሁ አለኝ። ሁልጊዜ በመጽሐፉ ጀርባ ላይ የታተመ በመጽሐፉ ውስጥ ያልተጻፈ ነገር ይሆናል ብዬ አስብ ነበር፡ በአንጻሩ ግን እርሱ እንደዚያ እንደማይደርግ የታወቀ ሆነ። በመጽሀፉ ውስጥ የተጻፈ ነገር አይደለም… ይልቅ ግን በመጽሐፍ ውስጥ የተደበቀ ነገር ነው። “ከዚህ ላይ አንዲት ቃል የሚቀንስ ወይም በእርሱ ላይ አንዲት ቃል የሚጨምር ሁሉ… ” ስለዚህ በእነዚህ ሰባት የቤተ ክርስቲያን ዘመናት በመጽሐፍ ውስጥ የነበረው ምስጢር ነው። ስለ ውሃ ጥምቀት እና—ለረጅም ጊዜ ሲሳለቁባቸው ስለ ነበሩት፡ ስለ ሌሎች ነገሮች እያንዳንዳቸው አንድ በአንድ ምስጢር ያፈልቃሉ።

84 ከዚያም ከፍ እያለ ሲወጣ፡ ከካሊፎርኒያ ጀምረው፡ እስከ ሜክሲኮ፡ በቱሰን፡ በየሰፍራው የተተከሉ መቆጣጠሪያ ጣብያዎች፡ በሁሉም ቦታ፡ ፎቶውን ሲያነሱ ነበር። ምስጢራዊ እይታ ነበር። ከዚያም ወደላይ ሲወጣ፡ ወንድም ፍሬድ ሶትማን፡ ማዶ ላይ ከኋላ ቁጭ ብሎ ነበር፡ እኔ እና ወንድም ጂን ኖርማን በዚያ ቆመን ነበር። ፎቶውን አንስተውታል፡ አሁንም ስለ እሱ ምንም አያውቁም። ከተወሰነ ጊዜ በፊት፡ ሰው ሁሉ እንዲህ ይላል ነበር፡ “ይሄኛው **እንዲያ** ይመስላል፡ እነዚያም የመላእክት ክንፎች፡ እንዴት እንደታጠፋ። እዚያ ጋ ተመልከተው።”

85 አንድ ቀን ግን፡ ወደ ቀኝ በኩል ዞሮ፡ በታየ ጊዜ፡ ሆፍማን እንደሳለው የኢየሱስ ክርስቶስ ምስል እነሆ ታየ። እርሱ ሉአላዊ ባለስልጣን መሆኑን የሚያሳይ፡ ነጭ ዊግ ራሱ ላይ አድርጎ፡ ፊቱ ወደ መሬት ኣዞሮ ቆሞ ነበር። ሰማያት ተናገሩ፡ መጽሀፍ ቅዱስ ተናገረ፡ መልእክቱም ተናገረ፡ ሁሉም በአንድነት። ነጭ ዊግ ያጠለቀ፡ ሉአላዊ ባለስልጣን፡ ከሰር ያለው ጥቁር ጺሙን አይታችሁታል። ብዙዎቻችሁ ስዕሉን አይታችኋልና። እዚያ ማዶ ላይ ሰቅለነዋል። በጎኑ በኩል፡ ወደ ቀኝ አዙራችሁ፡ ተመልከቱት። ልክ ነው፡ ፎቶ ግራፍ ተነስቶ ቢሆን ኖሮ፡ በትክክል እሱን የሚመስለው ይህ ነው። እነሱ ከተሳሳተ አቅጣጫ እየተመለከቱት ነው። በትክክለኛው አቅጣጫ ሆናችሁ ማየት አለባችሁ። ትክክለኛው አቅጣጫ መግለጥ የሚችል ግን ጌታ እግዚአብሄር ብቻ ነው። ወደ ቀኛችሁ በኩል አዙራችሁ ተመልከቱት። እሱ ይሄው ነው፡ በዚያ፡ እንደተነሳው ፍጹም ምስል።

86 እኔ እሱን የመጀመርያ ቀኔ ሳየው፡ **የሆፍማን...** ራስ ይመስላል። ከዚያ በፊት ስዕሉን አይቼው አላውቅም ነበር። ከዓመታት በኋላ፡ በወንድም ስንደይስ ተበርናክል፡ አየሁት። ቤቴ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እነዚህ ስዕሎች የሌለበት ሆኖ አያውቅም።

87 ከዚያ፡ አሁን የትምህርት ቤት ክፍሎች በታነጹበት አካባቢ፡ ህጻን ልጅ በነበርኩ ጊዜ፡ በራእይ አየሁት ያልኩት ያው አምላክ ልክ በሰማይ ላይ ያየሁትም፡ እሱን ይመስላል። አሁን ደግሞ፡ ከሠላሳ-ሦስት አመታት በኋላ፡ እነሆ ሰማያት ተናገሩ፡ ይህ እውነት ነው። መልኩ ያ ነው፡ የሆነ ሰው የሚያስበው ምስጢራዊ እና ሐሳባዊ ምስል የለውም።

88 ለምሳሌ በቫቲካን፡ ክርስቶስን የሳሉበት ሰ—ሰ—ሰዕል አላቸው፡ ትንሽ የጠጉር ቀለበት ወይም ርዝመቱ ግማሽ ኢንች ያህል፡ በአገጩ ዙሪያ ነጭ የጢም ቀለበት ያለበት፡ በላይኛው የአፉ ዙሪያ ላይ **እንደዚህ** ጣል ያለበት፡ ክርስቶስን ነው ብለው ይጠሩታል።

89 ይህ በአንድ ወቅት በአንድ ጥንታዊ ካቴድራል ውስጥ የአዳም እና የሄዋን ምስል ይህ ነው በማለት፡ አንድ ግሪካዊ አርቲስት፡ አውሬዎች አስመስሎ የሳላቸውን ሰዕል ያስታውሰኛል። ሥጋዊ አእምሮ ስለ መንፈሳዊ ነገሮችን ያለው ግንዛቤ ይህ ነው። አዳም እስከ ዛሬ ከኖሩት ሰዎች ሁሉ እጅግ በጣም ቆንጆ ሰው ነበር፣ ሔዋንም በሁሉም መመዘኛ ፍጹም ሴት ነበረች ብዬ አስባለሁ።

90 ሥጋዊ አእምሮዎች ግን የነገሮች ሐሳብ የራሳቸው ግንዛቤ ያስቀምጣሉ፣ ከዚያም እግዚአብሔር ነገሩን በገዛ ኃይሉ አውርዶ ግልጽ ያደርገዋል። በአክዓብ ዘመን የነበረው ነገርም ይኸው ነው።

91 እንግዲህ፡ የዘመኑ መልእክት እና የእግዚአብሔር ቃል፡ ወይም፡ መልክተኛው፡ መልእክቱ—መልእክቱ፡ እና ቃሉ፡ አንድ ሰለነበሩ፡ ኤልያስ ይህን ሊል እንደቻለ ተረድተናል። ነቢዩ፡ ቃል፡ መልእክቱ፤ መልእክተኛው፡ መልእክቱ፡ እና መልእክቱ፡ ያው ነበሩ። ኢየሱስም "ስለ እኔ የተጻፈውን ካላደረግሁ፡ አትመኑኝ፡" አለ። መልካም ነገር ነው። ማንኛውም ሰው እና መልእክቱ አንድ ነው።

92 ዛሬ የእግዚአብሔርን ሥራ በመሥራት የማያምኑት ለዚህ ነው፡ ምክንያቱ የእግዚአብሔርን መልእክት አልተቀበሉትም። መልእክቱን አላመኑበትም።

93 የምንኖርባትን የእግዚአብሔርን ሰዓት ላመኑት ግን፡ እነዚህ ነገሮች የተደበቁ ምግቦች ናቸው። እሰቲ አሰቡት፡ እግዚአብሔር እየተመለከቱት እንደማያዩት አድርጎ ደብቆታልና አያዩትም። ኤልያስም የሶርያን ጦር በተመሳሳይ መንገድ አሳወረ። እግዚአብሔርም የልጅ ወይም የአማኝ ትክክለኛው እንጀራ እንዲያዩ የማያምኑትን በተመሳሳይ መንገድ አሳወራቸው።

94 መርከብ በመሰራቱ፡ "ወግ አጥባቂ፡" ብለው የጠሩት ኖህ፡ ዓይኖቹ ዓይኖቹ ለእግዚአብሔር ቃልና ለተሰፋው ቃል ተከፍተው ነበር። ወግ አጥባቂነት ብለው የጠሩት ነገር፡ ኖኅንና ቤተሰቡን አዳነ። አያችሁ፡ ያው ተመሳሳይ ነገር ነው። ሰዎች የሚሳለቁበት ነገር፡ እኛ የምንጸልየው ለሱ ነው። ሰዎች "እብደት" የሚሉት፣ እኛ "ክብር!" እንለዋለን። ዓለም "ክብር" ብሎ የሚጠራው ነገር፡ በእግዚአብሔር ዘንድ "ሞኝነት" ነው። ለዓለም "ሞኝነት" በእግዚአብሔር ዘንድ "ክብር

ነው!" በእውነት እና በስህተት መካከል ያለው ንፅፅር ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።

95 አስታውሱ፡ በእግዚአብሔር እቅድ፡ በእግዚአብሔር ጥሪ፡ እና በእግዚአብሔር ቃል ወደ ሚስጥራዊው ቦታው ሄደ። በእግዚአብሔር አስቀድሞ ማወቅ እቅድ፡ እንደ እግዚአብሔር ቃል፡ በህይወቱ በነበረው ጥሪ ምክንያት፡ ኤልያስ ወደ ሚስጥራዊ ቦታው ገባ። እኛም የምንገባው በዚህ መንገድ ካልሆነ፡ እንዴት መግባት እንደምንችል አላውቅም።

96 አስተውሉ፡ ድርቁ ከመጀመሩ በፊት፡ ኤልያስ ለመኖር ወደ ሚስጥራዊው ስፍራ ሄደ። ፍርድ በምድር ላይ መምታት ከመጀመሩ በፊት፡ ቤተክርስቲያን አስቀድማ ተጠርታ፡ ሙሽራዋ ቀድሞውኑ ተመርጣ፡ በፍርድ ከመምታቱ በፊት እየተጠባበቀች ትገኛለች። የእግዚአብሔርን ምግብ እየበላች፡ በእግዚአብሔር በረከቶች እየተደሰተች፡ በመጠባበቅ ላይ ናት። ጤነኛ አእምሮው ያለው ሰው እንዲያው ወደ ፍርድ ሰዓት አፋፍ፡ በቀጥታ እንደተነዳን ያውቃል።

97 እዩ! ወንድም ባንክስ፡ እና በዚያች ማለዳ በተራራው ላይ ቆማችሁ የነበራችሁ፡ ዛሬ እዚህ የተገኛችሁ ሰዎች።

98 ጌታ ቢፈቅድ፡ በሚቀጥለው እሁድ ጠዋት፡ ስለዚያ ተራራ መናገር እፈልጋለሁ። በዚህ ምሽት ከመናገር ልቆጥበው የማልችለው ተጨማሪ ነገር፡ ታላቅ መገለጥ አግኝቻለሁ። ይሁን እንጂ... አያችሁ? እና ደግሞ ያለማቋረጥ፡ በተደጋጋሚ፡ አንድ ነገር ሌላውን በማስከተል የተከሰተ ነገር ነው። አያችሁ? **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ስለሆነ፡ መፈጸሙ በፍጹም አይቀርም።

99 እዚህ ያላችሁ ሁላችሁ፡ በቴፕ የምታዳምጡ ሺህ ጊዜ ሺህ የሆናችሁ፡ ቆሜ ስናገር እንዲህ ሰል ሰምታችኋል፦ "**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**፡ **እንዲህ** እና **እንዲያ** ይሆናል።" ጋዜጦች እና መጽሔቶች እንኳን እንደዛው እውነት መሆኑን አውጀዋልና። ምን ማለት እንደሆነ አያውቁትም፡ ይሁን እንጂ አይተውታል። ምን እንደሆነ አያውቁትም እንጂ፡ አይተውታል፡ ቃሉንም በትክክል እውነተኛ አድርጎታል።

100 በዚያ ቀን የእግዚአብሔር መልአክ በወረደ ጊዜ፡ እኛ ሁላችን በዚህ በወንዙ ዳር ቆመን ነበርን፡ የዛሬ ሠላሳ-ሦስት ዓመታት፡ በፊት፡ በ1933 ነበር፡ ወርዶም ያደረጋቸውን ነገሮች ሁሉ ተናገረ። ከወጣሁ በኋላ፡ በዳርቻው ላይ ቆመው የነበሩ ሰዎች፡ "ቢሊ፡ ይህ ምን ማለት ነው? " ይሉኝ ነበር፤

101 "ስለ እናንተ እንጂ፡ ስለ'ኔ አይደለም። እኔ አምኛለሁና፡ እናንተ ግን አላመናችሁም፡" አልኳቸው። እና መንገዴን ቀጠልኩ።

102 ከዚያም ፓስተሩ፡ እንዲህ አለኝ፦ "ማለት አንተ የሰባተኛ ክፍል ትምህርት ይዘህ፡ ለገዢዎች እና ለባለ ሥልጣናት እንዲሁም ለነገሥታት እና ለሌሎች ልትጸልይ ወደ ዓለም ሁሉ ልትሄድ? ኧረ፡ ባክህ፡" እንደው፡ "እርሳው አለኝ!"

103 አልረሳውም፡ በልቤ ላይ ተቀርጾ ቀርቷል። አሁን እዚህ፡ ከሠላሳ-ሦስት ዓመታት በኋላ፡ አደርገዋለሁ ብሎ የተናገራቸው ነገሮች ሁሉ እሱ እንደተናገራቸው በትክክል ተፈጽሟል። አምላክ ነውና አይስናከልምና። ቃሉን ሁሌ ይጠብቃል። በፍጹም... ተጠርጥሮ አያውቅም።

104 አሁን፡ አስተውሉ፡ በእግዚአብሔር እቅድ (በቅድመ-ማወቅ፡) በእግዚአብሔር ጥሪ፡ እና በእግዚአብሔር ቃል፡ ድርቅ ሳይጀምር እሱ ገባ።

አሁንም፡ ፍርድ መምታት ለመጀመር እንደተዘጋጀ አውቀናል።

105 በዚያ ቀን ኮረብታው ላይ ሆነን፡ ወንድም ባንክስ ዉድ እዚህ ቆሞ፡ ወደ ኮረብታው ላይ እየወጣን ነበር። ምናልባት በሚቀጥሉት አሰር፣ አስራ አምስት ደቂቃዎች ውስጥ ለሚካሄደው ለዚህ የፀሎት መስመር እምነታችሁ እንዲበረታ፡ እንደገና እጠቅሳለሁ። ወንድም ባንክስን ቀድሜ ፊት ፊቱ እየሄድኩ ነበር። ይመስለኛል… እህት ሩቢን ታማ ትቷት እንደወጣ አስታውሳለሁ። እና ከኋላዬ እየመጣ፡ ፊቱን ሳየው፡ ቀልቷል። ወደ ኋላ ተመለከትኩ። ኮረብታው ለመውጣት ትንሽ ሊከብደው ይችላል ብዬ ሰላሰብኩ፡ ፍጥነቴን ቀነስኩ። በዚያ የእግዚአብሄር መላእክት **እንዲህ** በተከሰቱባቸው፡ በምድረ በዳዎች፡ በእነዚያ ኮረብቶች መካከል። ከጥቂት ወራት በፊት በተከሰቱባቸው በዚያ ስፍራ፡ ፊታችን ወደዚያ አቅጣጫ አድርገን እየተጓዝን ነበርን።

106 በተራራው ራስ ላይ በወጣሁ ጊዜ፡ የእግዚአብሄር መንፈስ… ዞር ስል፡ ከተራራው አናት ላይ አየሁ፡ እንዲህ አለኝ፡- "ያንን ዓለቱን አንሳና፡ 'የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር እንዲህ ይላል፡ በሚቀጥሉ ጥቂት ሰዓታት የእግዚአብሔር ክብር ታያለህ።' በለው አለኝ።"

107 ድንጋዩን አንሰቼ፡ እንዲህ አልኩት፡- "ወንድም ባንክስ፡ ለምን እንደሆነ አላውቅም፡" ወደ አየር ወደ ላይ ወረውርኩትና፡ እንዲህ አልኩት፡- "የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር እንዲህ ይላል፡ የእግዚአብሔርን ክብር ታያለህ።"

"ሩቢን ማለትህ ነው? " አለኝ፤

108 እኔም አልኩት፡- "አይ፡ ከባንክስ ወይም ከሩቢ፡ ከማናችሁም ጋር፡ የሚገናኝ ነገር አይመስለኝም። በቃ አባባል ሆኖ እንደሚመስለኝ፡ 'የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር እንዲህ ይላል፡ የሆነ ነገር ይፈጸማል ነው።'"

109 እና በማግስቱ ጠዋት እዚያ ቆመን፡ ከወንዶቹ ብዙዎቹ፣ አሁን ምን ያህሎቹ እዚህ እንዳሉ አላውቅም፡ በዚያ አሥራ ሁለት ወይም አሥራ አራት፡ አሥራ አምስት ሆነን ተቀምጠን ነበር። ድንገት፡ አንድ አገልጋይ ወደ እኔ ቀረበና እንዲህ አለኝ፡ "ወንድም ብራንሃም፡" "ስሜ **እከሌ-እና-እከሌ**፡" እባላለሁ አለኝ። "ካሊፎርኒያ ውስጥ ስፖንሰር ካደረጉህ ሰዎች አንዱ ነበርኩ፡" አለኝ።

110 እኔም፡ "ስለ አወቅኩህ ደስ ብሎኛል፡ ጌታዬ።" ዳግላስ ማክሂዩስ። "እኔም… " አለ፤ "ስለተዋወቅኩህ ደስ ብሎኛል፡" አልኩት። እጅ ተጨባበጥን።

111 አለኝም፡- "እንግዲህ፡ አሁን፡ የምጠይቅህ ጥያቄ አለኝ።" አለኝ… ባለአደራው፡ ሮይ ሮበርሰን፣ ወንድም ዉድ፣ ቴሪ እና ቢሊ፣ ኦህ፡ እነ፡ ወንድም ማክ አናሊ፡ ሌሎች እነማን ነበሩ አላስታውሰም ቆመን ነበር። እና… አለ፡- "ልጠይቅህ እፈልጋለሁ።" "ጌታ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ራእዮችን ሰጥቶህ ያውቃልን? " አለኝ፤

112 እኔም "አዎን፡ ወንድሜ፡ እኔ ግን ከሱ ለመራቅ፣ ለማረፍ ወደዚህ መጣሁ፡" አልኩት።

እና **እንዲህ** ዞር ብዬ ተመለከትኩና፡ ገዘፍ ያለ ዶክተር ጠጋ ብሎ እያየው፡ እንዲህ ሲለው አየሁት፡ “ሬቨረንድ፡ ማክሂዩስ፡ ይህ በአይንህ ውስጥ ያለው አለርጂ በቅርቡ ዓይንህን ያሳጣሃል። ለሁለት ዓመታት ያህል ሕክምና ሰጥቼሃለሁ፡ ምንም ማድረግ አልቻልኩም።”

ወደ’ሱ ዘወር አልኩና። “ይህ ጥያቄ እኔን የጠየቅክበት ምክንያት፡ በቀደም ለት፡ ‘አይንህ ውስጥ አለርጂ አለ፡’ ብሎ ዶክተርህ ስለተናገረህ ነው፡” አልኩት። ከቀኑ አምስት ሰዓት፡ ገደማ ነበርና፡ አይኑ ላይ መነጽር አድርጎ ነበረ። አልኩትም፦ “ያንን ያላደረግክበት ምክንያት፡ በዓይንህ ምክንያት፡ ጸሀይ ስለሆነብህ ነው። ሰውዬው ‘አይንህን ታጣለህ’ ብሎሃል አልኩትና።”

“እውነት ነው፡” እያለኝ፡ ማልቀስ ጀመረ።

113 እንደገናም ለመሄድ ዞር አልኩና፡ አካፋን በእጄ ይዤ ነበር። አየሁም፤ እነሆ አይኖቹ ደምቀው፡ ቆሞ ሲያየኝ አየሁት። “አይንህን አታጣም፡ **ይልሃል የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር**፡” አልኩት። ባለፈው የበልግ ወቅት አብሬው እያደንኩ ነበርና፣ ከእኔ እና ከህዝቡ በበለጠ ከማንም የተሻለ ማየት ይችላል። በጭራሽ...

114 አንዲት አሮጊት ሴት እስቶኪንጋቸውን አውርደው ወደ ቀሚሳቸው ጎን ከፍ ሲያደርጉ አየሁ። እንዲህ ብለው ተናገሩ፦ “ልጄ፡ ወንድም ብራንሃምን ካገኘኸው፡ ለእግሬ እንዲጸልይልኝ ንገረው።” ጠጋ ብዬ አየሁ፡ እነሆም... ዕጢ የመሰሉ ነገሮች በእግራቸው ላይ ተንጠልጥለው ነበረ።

115 እኔም፦ “እናትህ ጸጉረ-ሽበታም እመቤት ናቸው። አየህ፡ ‘ልጄ።’ ከመምጣትህ በፊት፡ እኔን ካገኘኸኝ፡ ሰለ እግሯ እንድጸልይላት ጠይቅልኝ ብላሃለች። በእግሯ ሁሉ፡ እንደ ተንጠለጠሉ የሚመስሉ፡ ትንንሽ ዕጢዎች አለባት።” አልኩትና ራሱን ሊስት ትንሽ ነበር የቀረው።

“ይህ እውነት ነው፡” አለ።

“እንዳትጨነቅ ንገራት፡ ደህና ይሆናል በላት፡” አልኩት።

116 ጉዞዬን ቀጠልኩ። የእግዚአብሔር ድምፅም፡ እንዲህ ሲል ሰማሁ፡ “በፍጥነት፡ ከዚህ አካባቢ ራቅ።”

ሮይ ሮበርሰን እዚያ ቆሞ ነበርና፡ የጦር አርበኛ መሆኑን ስለማውቀው፡ እጄን ትከሻው ላይ አድርጌ፦ “ወንድም ሮይ፡ በተቻለህ ፍጥነት፡ ተደበቅ!” አልኩት፤

“ምን ተፈጠረ? ” አለኝ፤

“ራቅ እና አምልጥ! ተደበቅ!” አልኩት።

117 ገና ጉዞ መጀመሬ ነበርና፡ አካፋየን ወደታች አድርጌ፡ ኮፍያዬን አውርጄ፡ ዞር አልኩ። እነሆም የእግዚአብሔር ክብር፡ በዐውሎ ነፋስ ውስጥ የተራራውን ጎን እንዲህ ሰንጥቆ መፍሰስ ጀመረ፡ ቦታዉን እንዲህ አናውጦ አንቀጠቀጠውና፡ የቊጥቋጦዎቹ እናት ቆራርጦ፡ ከጭንቅላቴ ሦስት ወይም አራት፡ አምስት ፊት በላይ ነበረ። እንደማንቆርቆርያ ወደ ላይ ተመልሶ ሄደና፡ እንደገና ተናወጠ። እነሆም፡ ሦስት ጊዜ፡ መጣ።

118 በሦስተኛው ጊዜ፡ ከሄደ በኋላ፡ ወንድም ባንክስ መጣና፡ “የነገርከኝ ነገር ይህ ነውን? ” አለኝ፤

“አዎን፡” አልኩት።

“ምንድነው? ” አለኝ፤

119 እኔም፡- “እግዚአብሔር በዐውሎ ነፋስ ውስጥ ታየን።” ለሰዎች እንድናገር ይፈልግ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ አላውቅም አልኩት።

120 ሄጄም ትንሽ ጸለይሁ። ከዚያም ልነግራቸው እንደምችል ነገረኝ። “ምእራባዊ ጠረፍን በፍርድ እየመታ ነው፡” ብዬ ተናገርሁ። ዛሬ ተመልከቷት! ነገሩ ከተፈጸመ ከጥቂት ሰዓታት በኋላ የሆነውን ተመልከቱ፡ አላስካ ሰመጠች። አሁን ነገሩ ሁሉ እየሰመጠ ነው። ምሕረት ተወግዷል። ወደ ፍርድ እየገባን ነው።

121 እኛ ግን እግዚአብሔር ይመስገን፡ በመጨረሻው ዘመን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በገዛ ህዝቡ መካከል እራሱን እያሳየ በመገለጡ ከሚገኝ ምሕረት እና ቸርነት፡ የተደበቀ ምግብ መንፈሳዊ ምግብ አግኝተናል። አሜን! ድርቅ ከመምጣቱ በፊት ኤልያስ ገባ። ተደበቁ። ፍርዱ ከመምጣቱ በፊት ስለገባን እግዚአብሔር ይመስገን። የመውጣት እና የመግባት ጊዜ አሁን ነው፡ ከተቋማት ወጥተን ወደ ክርስቶስ የምንገባበት ጊዜ ይህ ነው፡ ይህ ጊዜ እውነተኛ ለሆኑ አማኞች- ወጥተው ወደዚህ የሚገቡበት-ጊዜ ነው።

122 ስለዚህ እርሱ ተጠርቶ፡ በዚያ ቆየ። አስታውሱ፡ እግዚአብሔር እስኪጠራው ድረስ ጅረቱን ትቶ አልሄደም።

123 ድርቁም ካለፈ በኋላ፡ ከዚያ፡ ወደ አንዲት መበለት ቤት ጠራው። አስተውሉ፡ ወደዚች መበለት ጠራው። ይህችም መበለት ራሷን ከማያምኑት ጋር አላስቆጠረችም። በድርቅ ጊዜ የአውሬውን ምልክት አልተቀበለችም። ስለዚህ እርሷን ጠራ... ይህችን መበለት እንዲደግፍ ኤልያስን ጠራው። አንዲት ትንሽ እንጎቻ ብቻ ቀርታቸዋለች፡ ትንሽ ቁራሽ እንጀራ ይዛ ነበር። ኤልያስም፡ “አስቀድመሽ፡ ለእኔ ስጪኝ። **የሰራዊት ጌታ እግዜብሔር እንዲህ ይላልና**፡ በምድር ላይ ጌታ እግዚአብሔር ዝናብ እስከሚሰጥበት ቀን ድረስ፡ እህሉ ከማድጋ አይጨረስም፡ ዘይቱም ከማሰሮው አይጎድልም።” እግዚአብሔርን ማስቀደም፡ ቃሉን ማስቀደም!

124 አስተውሉ፡ ማድጋው ውስጥ ዱቄት አልጎደለም። እህል በፈለገች ቁጥር፡ ማድጋው ውስጥ እህል ነበራት። ዘይትን ፍለጋ በሄደች ቁጥር፡ ከማሰሮ ውስጥ አልጎደለም። ለምን? እህሉ ክርስቶስ በእህል-ቁርባን ላይ ይወክላል። እያንዳንዱን በደንብ ለመሰለቅ፡ ወፍጮው ዘወትር የተዘጋጀ መሆን አለበት። የዚህ ምግብ መፍጫ ሁሉ አንድ አይነት ነው፡ ይህም እሱ ትናንትና፣ እና ዛሬ፣ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው እንደሆነ ያሳያል። ቃሉን ያጸና ዘንድ፡ ከመልእክቱ በኋላ የሚከተል የሕይወት እንጀራ፡ የሆነው ቃል ነበር።

125 ዛሬም እንዲሁ ነው፡ ወዳጆች። ዛሬም እንዲሁ ነው፡ ልጆቹ የሚበሉት የሕይወት እንጀራ፡ በድርቅ ጊዜ እነርሱን ለማቆየት፡ የእግዚአብሔርን መልእክት ይከተላል። ዛሬ በፊታችን ቢቆምስ? አሁን በፊታችን ቢቆምስ? በዚህ ምድር ላይ በሥጋ በነበረበት ጊዜ እንዳደረገው ሁሉ ተመሳሳይ ነገር በሰራና ባደረገ ነበር። ሙሽሪት የባል አካል ናት፡ ቤተክርስቲያን እንደ ክርስቶስ ያው ነች። “እኔ የማደርገውን ሥራ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ።” እርሱ ያደረጋቸውን ስራዎች እኛ ደግሞ መስራት እንደምንችል ነግሮናል። ስራውን የሚሰራው ግን ቃሉ ነው።

126 በዚያ ቀን ቃሉ በኤልያስ ዘንድ እንደነበረ፡ ወደ እኛ ከመጣ በእኛ ውስጥም ከገባ፡ ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር ያደርጋል፡ ከዓለም የተሰወረው የእግዚአብሔር ምስጢራዊ ነገሮች ይመግበናል። ኦ! አሁንም፡ መልእክቱንና መልእክተኛውን አንድ ያደርጋቸዋል። መንፈሳዊው ምግቡ ዝግጁ ሆኗል፡ አሁን ወቅቱ ነው። ወደ ክርስቶስ ለመምጣት እና ወደ ተሰፋ ቃሉ ለመግባት ከተዘጋጀችሁ፡ በዘመኑ ካለው አለማመን ሁሉ ለመራቅ ፈቃደኞች ከሆናችሁ፡ እያንዳንዳችሁ ከፈለጋችሁ፡ ይህን ምግብ መመገብ ትችላላችሁ።

በሚልክያስ 4፣ ሉቃስ 17፡30፣ እንዲሁም በቅዱስ ዮሐንስ 14፡12፣ እና ሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት፡ በኢዩኤል 2፡38፣ ወይም 2፡28፣ የሚናገረው፡ እና የሚያደርገውን ሁሉ፡ ይልቁንም፡ በዚህ የመጨረሻ ቀናት ምን እንደሚያደርግ አስታውሱ። ነቢዩ በዚህ በመጨረሻው ዘመን ብርሃን እንደሚሆን፣ እንዴት እንደሚሰራ፣ ምን እንደሚያደርግ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ወደዚህ የመጨረሻ ቀን ያመላክታሉ ብሏል። እርሱም ክርስቶስ ነው! አሁን እናንተም በዚያ፡ በምስጢራዊው ቦታ ውስጥ መደበቅ ከቻላችሁ፣ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ምሕረት መብላትና ማየት ትችላላችሁ። ከታመማችሁ፡ በዚያ ፈውስ አለ።

127 ኤልሳዕ፡ በኋላ፡ ሲጠራ ታስታውሳላችሁ… ካቀረበው ከእህል-ቍርባን፡ ክርስቶስን ከያዘ በኋላ፡ የመበለቲቱን ቤት በእርሱ ደገፈ። አስታውሱ፡ በኋላ ከሰማይ እሳትን እና የመሳሰሉ ነገሮች፡ ባወረደ ጊዜ፡ በነብያት መንፈስ፡ ከእግዚአብሄር ዘንድ፡ የተላከ እንደነበረ አረጋገጠ።

128 አስታውሱ፡ በምድረ በዳ፡ ከጥድ ዛፍ በታች በተኛ ጊዜ፡ መልአክ ተመሳሳይ እህል ይዞ ወረደና፡ እንጎቻ ጋግሮ አበላው። እና ትንሽ ቆይቶ እንደገና አስተኛው፡ እና ቀሰቀሰው፡ እና እዚያ የተጋገረ የእህል እንጎቻ አዘጋጀለት። በዚያው ምግብ ኃይል ለአርባ ቀናት ተጓዘ። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን! እሱ ትናንትና፡ ዛሬም፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው። ኦ፣ ለሱ ያለን ፍቅር እንዴት ብዙ ነው፣ መንፈሳዊ ምግብ በጊዜው!

129 "የልጆቹን እንጀራ ወስደህ ለውሾች መስጠት ተገቢ አይደለም።" ኢየሱስ ለሲሮፊኒቃዊቷ ሴት ተመሳሳይ ነገር ተናግሮ የለምን? የራሱ ወደሆኑት መጣ። እውነት ነው። የመጣውም እርሱ… ፈጽሞ ወደ አሕዛቦች አልሄደም።

130 ዛሬም በጊዜያቸው አሕዛብን ጎበኘ፡ ስለዚህ አሁንም ተገቢ አይደለም…

131 እናንተም ትላላችሁ፦ "ለምንድነው መልእክቱ በእነዚህ ታላላቅ ቦታዎች፣ በእነዚህ ትላላቅ ክሩሴዶች፣ በሐማኖት ተቋማት መካከል ያልገባው? "

132 ምግባቸው አይደለም። ምግብ፡ የምትለው፡ ቤተክርስትያን አይደለችም። የሙሽራዋ ምግብ ነው። የጊዜው መንፈሳዊ ምግብ ነው። ሆዳቸው እንዲታመሙ ያደርጋቸዋል። እጅግ ይከብዳቸዋል። አያችሁ? አያችሁ? ይሄን ል—ል—ልታደርጉ አይቻላችሁም። ለልጆቹ ግን፡ እንጀራ ነው፡ ህይወት ነው፡ ትናንትናም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘለአለም ድረስ ያው የሆነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

133 የጸሎት መስመሩን አሁን ካልጀመርነው እጅግ ስለሚረፍድብን፡ ለአፍታ አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

134 አምላክ ሆይ፡ የጊዜው ምግብ፡ መንፈሳዊው ምግብ በጊዜው ነው። ዓለም ምንም የማያውቀው ነገር ነው። ጌታችን በዚያች ሌሊት ወይም በዚያች ቀን

በሰማርያ፡ ኤልሳዕ ወጥቶ እንዲህ ብሎ በተናገረባት፦ “እንደው፡ ከአፌ ቃል በቀር ጠልና ዝናብ አይሆንም።” ኢየሱስም ቆሞ ለደቀ መዛሙርቱ ሲነግራቸው ሰምተነዋል።

“መምህር፡ ለምን አትበላም? ” ባሉት ጊዜ፤

“እናንተ የማታውቁት ምግብ ለእኔ አለኝ፡” አላቸው።

135 በእውነት፡ የጌታ ምግብ፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ማድረግ፡ የእግዚአብሔርን ሥራ በዘመኑ ሲገለጥ ማየት ነበር። ሲፈጸም ለማየት በዚያ ነበረ። “አባቴ አስቀድሞ ካላሳየኝ በቀር ምንም አላደርግም። አብ የሚያሳየኝን ሁሉ፡ ማደርገው እሱን ነው።”

136 ዛሬም፡ አባት ሆይ፡ እንዲሁ ነው። ቤተ ክርስትያን፡ እውነተኞቹ አማኞች፡ የአማኞች አካል፡ ሌሎች ሰዎች ምንም የማያውቁት ምግብ፡ መንፈሳዊ ምግብ፡ የማግኛ ቁልፍ አላቸው። አባት ሆይ፡ ዓለም ስለዚህ ምግብ ምንም አያውቅም። ቤተ ክርስትያንህ፡ ህዝብህ፡ የልጅህ ሙሽራ ግን፡ ትወደዋለች።

137 ዶክተሮች መፈወስ የተሳናቸውን የስጋችን ፈውስ ማግኘት የምንችልበት ቁልፍ ይዘናል። ቁልፉ አለን። በመጨረሻው ቀን ለቤተክርስቲያኑ፣ እና ለሚያምኑት ልጆቹ፣ በዘመን ፍጻሜ ሊሰጥ ቃል ከገባቸው የእግዚአብሔር ምግቦች አንዱ ነው። አባት ሆይ፡ ለሚያምኑ ሁሉ ይቻላልና፡ የሚያምኑ ልጆች እንሆን ዘንድ እርዳን። አምላክ ሆይ፡ አድርግልን። በኢየሱስ ስም ጸለይን። አሜን።

138 ጥቂት የጸሎት ካርዶችን እንደሰጣችሁ ቢሊ ነግሮኛል። አንድ ሰው በጸሎት ካርዱ ላይ ያለውን ፊደል ቢነግረኝ፣ የምፈልገው ያ ብቻ ነው። [አንድ ሰው “ሲ፡” አለ።—እርታዒ።] ሲ፡ በጣም ጥሩ፡ አንድ፡ ለመጀመር ያህል፡ ሰልፋችን እስኪጀመር ድረስ። ሲ እንውሰድ፡ አያችሁ፡ አሁን፡ በየአቅጣጫው ይኖራሉ። አሁን፡ ሁላችሁም... ምናልባት፡ እንዲህ፡ እንዲሆን እሞክራለሁ። ማድረግ እንደምንችል ወይም እንደማንችል አላወቅኩም። እየጠራናችሁ ብትሰለፉ፡ ወይም ባላችሁበት ቁጭ ብትሉ። ለእኔ ለውጥ የለውም። ብትፈልጉ እዚህ መድረክ ላይ፡ ወይም እየጠራናችሁ ብትሰለፉ፡ ምንም አይደለም፡ ሁለቱም መንገድ ይቻላል። እኔ የምደገፈው በመንፈስ ቅዱስ ላይ ብቻ ነው። የሰበኩትን ይህን ቃል ለመጠበቅ በእርሱ እደገፋለሁ።

139 ወንድም ጆርጅ ራይት፣ አሁንም አምናለሁ። ከብዙ ዓመታት በፊት፡ ዊፑርዊል በዛፉ ላይ ተቀምጦ እየዘመረ፡ ትንሽ ልጅ ሆኜ ወደ ቤትህ ሰወርድ ጀምሮ፡ አሁንም ያንኑ መልዕክት አምነዋለሁ። ያው እንደሆነ አምናለሁ።

140 በጣም ጥሩ፡ ለጸሎት መሰመር እያመቻችሁ እንዳሉ ይታየኛል። እሺ፡ የጸሎት ካርድ ሲ፣ ቁጥር አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት፣ ቀድማችሁ እዚህ ቁሙ። መነሣት የማትችሉ ከሆናችሁ፡ እጃችሁን ብቻ ከፍ አድርጉላቸውና፡ መጥተው ይረዷችኋል። [አንድ ሰው ወንድም ብራንሃምን አናገረው—እርታዒ።] (ምንድነው? እሺ። ኧ-ሀህ) የጸሎት ካርድ ሲ፣ አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት። እናንተም የጸሎት ካርድ ያልያዛችሁ ልብ በሉ...

141 የዚህን አይነት የጸሎት መስመር ካደረግኩ ረጅም ጊዜ፡ ረጅም ጊዜ ሆኖኛል። ይህን ህንጻ ስንገነባ ተልእኮዬን የምታስታውሱ ሰንቶች ናችሁ? "የወንጌል ሰባኪን ሥራ አድርግ፡" አለኝ። ወንጌላዊ ነኝ አላልኩም። እየህ፡ "ይህ የሚቀየርበት ሰዓት ይመጣልና።" "የወንጌል ሰባኪን ሥራ አድርግ፡" አለኝ። ስለዚህ ያቺ ሰዓት ቀርባለች። በጣም ጥሩ። አሁን፡ በዚህ፡ ሁሉ...

142 ሁለት ወይም ሶስት የተለያዩ አገልግሎቶችን በአንድ ላይ፡ ፓስተር እና ወንጌል ሰባኪነት፡ በአንድ ጊዜ መቀላቀል አትችሉም። የተለያዩ ስራዎች፣ የተለያዩ አገልግሎቶች ስለሚኖርባችሁ፡ በተመሳሳይ ጊዜ—ነቢይ እንዲሁም ፓስተር፡ መሆን አትችሉም፡ አያችሁ።

143 ነገር ግን በመልእክቴ ውስጥ ማድረግ ያለብኝን ጌታ ሰጥቶኛል። በኋላ ግን እንዲህ አለኝ፦ "የወንጌል ሰባኪን ሥራ አድርግ፡ ጤናማ ትምህርት የማይታገሡበት ጊዜ ይመጣልና፡ የአገልግሎትህን ሙሉ ማረጋገጫ አድርግ።" ታዲያ አሁን ይህ አልመጣምን! የሐይማኖት ተቋማት በሙሉ ጀርባቸውን ሰጥተውኛል። ጤናማ ትምህርት መታገስ አይችሉም። "ነገር ግን የራሳቸው ምኞት እየተከተሉ የራሳቸውን አስተማሪዎች ያመጣሉ፡ ወደ ተረትም ዘወር ይላሉ። ኢያንበሬስና ኢያኔስ ሙሴን እንደተቃወሙት ታላቅ ሥራን ያደርጋሉ፡ ስንፍናቸው ግን ይገለጣል።" አያችሁ? አያችሁ? አዎን፡ ማስመሰሎች! ኢያንበሬስ ያደረገውን አይታችኋል...

144 እና፡ የሰማይ አምላክ ምስክር ነው፡ ይህ ሁሉ-... (የህንጻው)... -መሰረት ድንጋይ ላይ ከ1933 ጀምሮ የተቀመጠ ነው፡ እዚያው ተጋድሞ በተቀመጠ የመጽሐፍ ቅዱስ ገጽ ላይ፡ ተጽፎ ይገኛል። በትክክል፡ እንዴት እንዳስመሰሉ፡ እንዴት እንደሰሩት፡ ምን እንደሚሆን ተመልከቱት። "ተውአቸው፡ ስንፍናቸው እንደ ኢያንበሬስ እና ኢያኔስ ይገለጣል፡" አለ። እነሆ በዚያ ቀን ላይ ደረሰን።

145 ያን ጊዜ ቤተክርስቲያንን የማዕዘን ድንጋይ ስናስቀምጥ፡ ሰዎች ማማው ላይ እና በዙሪያው ሁሉ ላይ፡ በህንጻው ግድግዳ ዙርያ ላይ ቆመው አይ ነበር። ይኸውላችሁ። ግንባታው በወጣ ጊዜ፡ ተናገሩ፡ የከተማይቱ ሰዎች፡ እንዲህ አሉ፦ "በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ... " በአንድ ዶላር ከሰማንያ ሳንቲም ህንጻውን እየሰራን፡ የጋራጅ ባለቤት የሆኑ ብዙዎች ጋራጅ ለማድረግ ወስነው ነበር። ይሁን እንጂ እስከ አሁን ድረስ የእግዚ አብሔር በጎች በረት ሆኗል።

146 አንድ፡ ሁለት፡ ሶስት፡ አምስት፡ ስድስት፡ ሰባት፡ ሰምንት፡ ዘጠኝ፡ አስር። ሲ፣ ስድስት፣ ሰባት፣ ሰምንት፣ ዘጠኝ፣ አስር። እሺ።

147 አሁን፡ "እኔ እግዚአብሔር ተክዬዋለሁ፡ በቀንና በሌሊት አጠጣዋለሁ፡ ከእጄም አይወስድም።" ትችቱን ተመልከቱ! የሚደግፈው የሐይማኖት ተቋም የለም። በመላ አገሪቱ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ይሄን የሚወድ የለም። በአገሪቱ ያሉ ጴንጤቆስጤዎች፡ ይሄን ማቆየት የሚችል ነገር የለም። ሁሉም የውሃውን ጥምቀት ይቃወሙታል፣ ሁሉም እነዚህን ሁሉ ይቃወማሉ። በቤተሰቦቼ እንኳን፡ አባቴ ሳይቀር ከበሩ መለሰኝ፡ ልብሴን በትንሽ ወረቀት ከረጢት ውስጥ ወስጄ ኒው አልባኒ ሄጄ ኖርኩ። አዎን።

በብዙ አደጋዎች፣ ድካም እና ወጥመድ ግን፣
በቃ ወጥቻለሁ፡
ጸጋው እስከዚህ አድርሶኛል፡

ሐምሳ-ስድስት አመት ሆኖኛል፡ በቅርብ ወንዙን መሻገሬ የማይቀር ነው።

ጸጋው ያስቀጥለኛል።

አስር ሺ አመታት በዚያ እኖራለሁ፡
እንደ ጸሀይ ብርሃን ደምቄ
ለእግዚአብሔር ክብር የምንዘምራቸው ቀኖች አያንሱንም
መጀመሪያ ከጀመርንበት ጊዜ ይልቅ።

አቤት፡ ኢየሱሴን ሰወደው! እሱ ለእኔ ዓለሜ ነው!

148 ኦህ፡ እሺ፡ ሰንት አልኩ... ? ሰንት ላይ አቆምኩ፡ አሰር? ታዲያ ጥቂት እንጨምርበት? በጣም ጥሩ። ሰንት ነበር፡ አሰር፣ አሰራ አምስት? እሺ። ሲ፡ አሰር እሰከ አሰራ አምሰት፡ የትም ብትሆኑ፡ ተነሰታችሁ መምጣት ከቻላችሁ። ምን አልከኝ? ኧሀ? እሺ። ሲ፡ አሰራ አምሰት እሰከ ሀያ፡ እሺ። ሲ፡ ከአሰራ አምሰት እሰከ ሀያ ድረሰ ይሁን። ይህ ማለት አሰር ተጨማሪ ሰዎች ማለት ነው። እንዳየነው... መሰመሩ የት እንደደረሰ አ—አይታችኋል፡ ሰብሰባውን ሁሉ ማዳረሰ—አንችልም። እሺ... የቻልነውን።

149 አሁን ያልተከፋፈለ ትኩረት ሰጡኝ፡ ብዙ አንቆይም። አሁን፡ ግን፡ ኦህ፣ ድንቅ ጊዜ፣ ግሩም ጊዜ ነው! ሁሉም ሰው ጌታን እንዲወድ እ—መኛለሁ። የዚህን ደቂቃ አቅም ለመገንዘብ ሁላችንም ወደዚያ ሁኔታ እንድንመጣ እ—ናፍቃለሁ። እሰቲ እንሞክረው። ትኩረታችሁን ብቻ ሰጡኝ።

150 ምን ለማድረግ—እየሞከርን ነው? የእግዚአብሔርን ቃል በፈተና እያሳለፍን ነን። ኤልያሰም እንዲሁ አደረገ፣ ያደርግ ዘንድ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደተላከ ካወቀ በኋላ ወደ ተራራው ወጣ። "አምላክ ማን እንደሆነ እናረጋግጥ፡ በእሳት የሚመልሰ አምላክ እርሱ እግዚአብሔር ይሁን፡" አለ።

151 ጣኦት አምላኪዎቹ ራሳቸውን እየቆረጡ፡ ኦህ፡ "እንዴ፡ ይሁና፡ አይ... " ይሉ ነበር፤ ጣኦት አምላኪዎቹ—እሳት እንደማይወርድ ሰላወቁ፡ ይጮኹና ይንቀጠቀጡ ነበር።

152 ኤልያሰ ግን ከጌታ ዘንድ ራእይ አይቶ ሰለነበረ፡ እሳት እንደሚወርድ አውቋል።

"ራእይ አይቷል፡" ነው ያልከው?

153 የሰ ሰር! ሁሉንም ነገር በሥርዓት ካደረገ በኋላ፡ እንዲህ አለ፦ "ጌታ ሆይ፣ ይህን ሁሉ ያደረግሁት በትእዛዝህ ነው።" ከዚያ በኋላ እሳቱ መውረድ ጀመረ። የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ከታዘዛችሁ፣ ቀሪው ሰራ የእግዚአብሔር ጉዳይ ነው። እሱ እንዲህ አርገህ ሰራ ብሎ ይጠይቅሃል። አንተም እንደዚያው አርገህ ለማሰቀመጥ እንደተጠራህ ብቻ እርግጠኛ ሁን። አያችሁ? እንዲሁ ከሆንክ ደግሞ፡ ሌላው ራሱ ይሰራዋል።

154 አሁን፣ የምጸልይላቸው ሰዎች በዚህ መሰመር ወደዚህ ይመጣሉ... ሰለዚህ፡ አሁን፡ ለመጀመር ጥግ ደርሳችኋል፡ እሺ፡ ወደ መሰመሩ ተቃርባችኋል። አሁን፣ ለመጀመር፣ እሰኪ ቢያንሰ እዚህ ሕንፃ ውሰጥ፡ ካላችሁ ሰዎች...

የታመማችሁ ነገር ግን የጸሎት ካርድ ያላገኛችሁ ሰዎች፡ እጃችሁ ወደ ላይ አርጉ። አያችሁ፡ በቃ ሞልቷል። እንደው፡ ጌታችን ቢፈቅድ... መቼም እሱ ትላንት፡

እና ዛሬ፡ እና ለዘላለም ያው ስለ ሆነ፡ እንደሚፈቅድ አምናለሁ። እሱም የጸሎት ሰልፎች ያደርግ ነበር። ሰዎች በረዣዥም ሰልፎች፡ እና በብዛት እየመጡ፡ እሱ ይዳስሳቸው፡ እና ይባርካቸው ነበር። እንደው አንድ ቀን ቆም አለና “የነካኝ ማን ነው? ” አላቸው፤ ዙርያውን አይቶ፡ አንድ ሴት ለምን እንደነካችው፣ የደም ችግር እንደነበራት እና እንደተፈወሰች፡ እምነቷ እንዳዳናት ነገራት።

155 ዞር ብላ “ጌታ ሆይ፡ እንደው፡ እኔ አላውቅም፡ ይህ ነገር ከረጅም ጊዜ ጀምሮ አብሮኝ የቆየ ነገር ነው” ብትልስ ኖሮ? ባልሆነላት ነበር። በጭራሽ፡ አይሆንም ነበር። በጭራሽ።

156 ለሲሮፊንቃዊቷ ሴት እንዲህ ቢላትስ ኖሮ፦ “ሴት ልጂሽ በተናገርሽው በዚህ ቃል ምክንያት፡ ዲያብሎስ ከእርሰዋ ወጣ፡” እሷ ግን፦ “ጌታ ሆይ፡ እንደው፡ አሁን፡ እ—እኔ **በዚህ** መንገድ እንድታደርግልኝ እፈልጋለሁ”? ዲ—ያብሎስ በልጇ ውስጥ በቀረ ነበር። እሷ ግን ልጂሽን ትሆናለች እንዳላት እንደምትሆንላት ጠብቃ ሄደች።

157 እንግዲህ፡ እርሱ እንዳለ፡ “ብታምኑ! በልባችሁም ባትጠራጠሩ፡ እና ተራራውን ‘ተነቀል’ ብትሉት፡ የተናገራችሁት ነገር እንደሚፈጸም ብታምኑ፡ ይሆንላችኋል። ስትጸልዩ፣ እንደተቀበላችሁ እመኑ፣ ታገኙማላችሁ።” እንዴት ያለ ቃል ኪዳን ነው!

158 ሶሺያል ጎስፔል የሚሰብክ ሰው ይህን በፍጹም አያምንም። በር ድረስ ይጠጋል፡ ከዛ ይቆማል፡ ወደ ውስጥ አይቶ፡ እንዲህ ይላል፦ “አይ፡ ሌሎች ወንበር ሰባሪዎች ናቸው፡” ይልና ይሄዳል። አያችሁ? የተደበቀው ምግብ መሆኑን ግን አያውቅም። የተሰወረበት ምስጢር ይህ እንደሆነ አያውቅም። አያውቅም። በጣም—የ—ሚያሳዝን ነው፡ የተራቆተ፣ ጎስቋላ፣ እና ዕውር አእምሮ ነው፡ ግን አያውቀውም። አያችሁ? እጅግ የከፋ ነገር ይህ ነው።

159 አምላክ ሆይ፡ እንድሞት ፍቀድልኝ፡ እንጂ እንደዚያ እንድሆን ግን አታድርገኝ። ያንን ከማድረግ ብሞት እመርጣለሁ (የሰ፡ ሰር)። ሁላችንም ሞት እንመርጣለን ብዬ እሰባለሁ፡ አይደል?

160 ነገር ግን፣ አሁን፣ እግዚአብሔር በመጨረሻው ዘመን እነዚህን ነገሮች ቃል ገብቶልናል። ሚልክያስ 4 ላይ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰዶም እንዳደረገው በሰው ሥጋ እንደሚወርድና ራሱን እንደሚተርክ ተናግሯል። ትክክል ነው። እንዲሁም አለም በሰዶም እንደነበረ ሁኔታ ውስጥ እንደምትሆን ተናግሯል። “በዚያን ጊዜ እንደ ነበረ፡ የሰው ልጅ በዚያ ቀን ይገለጣል፡” አለ። አያችሁ፡ የተሰፋ ልጅ ከመምጣቱ በፊት፡ በአብራሃም ዘንድ፡ “ኤሎሂም” የተባለው፡ በሰው አምሳል የወረደውን ይህ ሰው ነበረ። ምን እንደነበረ ተመልከቱ፡ አብራሃም አምላክ ነው ብሎታል። መጽሐፍ ቅዱስም፡ ልብሳቸው ትብያ የጠጣ፡ ሦስት ሰዎች ወደ እርሱ ተጉዘው መጥተው፡ እንደሰው ቁጭ ብለው ምግብ እንደበሉ ይናገራል። ኢየሱስም አለ፦ “ዓለም የሰዶም ሁኔታ ውስጥ በምትገባበት ወቅት፣ ያን ጊዜ የሰው ልጅ ዳግመኛ ራሱን ይገለጣል።” አያችሁ፡ ራሱን የሚገልጠው፡ የሰው ልጅ እንጂ፡ የእግዚአብሔር ልጅ አይደለም።

161 እንግዲህ የኋለኛው ነቢይ በተናገረው ነገር ልብ በሉ፦ “እነሆ፡ ነቢዩን ኤልያስን እልክላችኋለሁ፥ እርሱም—የልጆችን ልብ ወደ አባቶች ይመልሣል።” አያችሁ? ወደ መጽሐፍ ቅዱስ የሚመልሳቸው መልእክት ነው፣

በዚያም ዘመን የሰው ልጅ ራሱን ይገልጣል። በዚያም የሰባተኛው መልአክ፡ የኋለኛዋ ቤተክርስቲያን ድምጽ በሚሰማበት ቀን፡ የእግዚአብሔር ምሥጢሮች ይገለጣሉ። ሰባቱ ማኅተሞች ይፈታሉ። የእነዚህ ሁሉ የአብያተ ክርስቲያናት ምስጢሮች፡ እንዴት እንደመጡ፣ እና ምን እንደተደረገ... እንዴት፣ እና ምን እንደተከሰተ ይገለጣል።

162 አያችሁ፡ አያውቁትም። ኢየሱስም "እናንተ ዕውሮች ፈሪሳውያን!" አላቸው፤ "ዕዉር ዕውርን ቢመራ፡ ሁለቱም ወደ ጉድጓድ ውስጥ አይወድቁምን? " ብሏል፤ አያችሁ፡ ሰዎቹ ይሄን ማየት የሚሳናቸው ለዚህ ነው።

163 የእነዚያ ማኅተሞች፡ ምስጢሮቻቸው፡ እያንዳንዳቸው አብያተ ክርስቲያናት ተቋም መሥርተው በዚያ መወሰዳቸው፡ ነው፡ ይህም በእግዚአብሔር ፊት ከተደረጉ ምስጢራዊ ነገሮች አንዱ ስሕተት ይህ ነው። አየህ፡ ዶክተር ሊ? አየህ፡ ተመልከት። ይሄው ነው። ነገሩ ያ ነው። ከምስጢሮቹ አንዱ ይህ ነው። አየህ፡ እንደ ተቋም ተደራጁ፡ ይህም ሙሉ ለሙሉ ከእግዚአብሄር ፈቃድ ውጪ ነበሩ። ይህም በመጨረሻው ቀን ይጋለጣል፡ ህዝቡንም፡ ወደ አዋልድ ወይም ወደ ሐይማኖት ተቋም ሳይሆን፡ ወደ እውነተኛው ቃል ይመራቸዋል። እውነተኛውም ቃል ወደ ጥቂት ሰዎች ይመጣል፡ የሰው ልጅም በመካከላቸው፡ "ትላንትና፡ ዛሬ እና ለዘላለም ያው እንደሆነ፡" እራሱን ይገለጣል።

164 ኦህ፡ ማይ! ኦህ፡ ወደድኩት። በርሱ—በርሱ መመካት እወዳለሁ። በሕዝቡ ፊት እርሱን ታላቅ ማድረግ—እወዳለሁ። እሱ አስቀድሞ ትልቅ ነውና፡ እሱን ትልቅ ማድረግ አይጠበቅብኝም። እርሱ በጣም ከፍ ያለ ነው ልትደርሱበት አትችሉትም፡ በጣም ዝቅ ያለ አትገቡበትም፡ በጣም ሰፊ ነው፡ አትደርሱበትም፣ በዚህ ሁሉ ግን በልባችሁ ውስጥ ለእርሱ የሚሆን ስፍራ አላችሁ። አትቀበሉትምን? አቤቱ ጌታችን እንዴት ድንቅ ነው! መልካም።

165 አሁን ሁላችሁም ዝም እንበል። አሁን ስለዚህ ጉዳይ ተነጋግረንበታል። እና አሁን ነገሩ፡ ነገሩ እውነት ነው አይደል? ምናልባት፡ በመካከላችን እንግዶች ሊኖሩ ይችላሉ። እስኪ እንዲህ ልበላችሁ... ክርስቶስ ለእናንተ፡ ትናንትና፣ ዛሬ፣ እና ለዘላለም ያው ከሆነ በዚህች ደቂቃ ምን ባደረገ ይሆን? ከዚህ በፊት እዚህ በነበረበት ጊዜ ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር ያደርጋል። ልክ ነው? የሰዎች እምነት ልብሱን ይነካዋል፡ እርሱም ዞር ባለ ነበር። በውኃ ጉድጓድ ላይ ከሴትዮዋ ጋር እንዳደረገው፡ በሌሎች ቦታዎችም አደረገ፡ የልብ ሀሳባቸውን አነበበ።

አሁንም እናንተ፡ "አሁን ሊፈውሰኝ ይችላልን? " ትላላችሁ፤

166 ቃሉ ግን አስቀድሞ እንደፈወሰን ተናግሯል። ቃሉ አስቀድሞ ያንን እንዳደረገ ተናግሯል። ዋናው ነገር እዚህ እንዳለ እራሱን ማሳወቁ ነው።

167 አሁን፡ ደም ከእጁ እየፈሰሰ፣ በሚሰማር ጠባሳዎች፡ እና በመሰል ነገሮች፡ **እንደ ሠላሳ-ሦስቱ የሆፍማንን የክርስቶስ ራስ መስሎ፡** በሥጋዊ አካል ቢገለጥልን፡ አልቀበለውም። አይ፡ አይ። አይ፡ አይ። እርሱ ራሱ ሲመጣ፡ "ዓይን ሁሉ ያየዋል፣ ምላስም ሁሉ ይመሰክርለታል፡ መብረቅ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ እንደሚመጣ፡ እንዲሁ ይሆናል።" አያችሁ? የአምልኮ ሥርዓቶችን እና ጎራዎችን አናምንም። እግዚአብሔር ቃል ነው ብለን እናምናለን።

168 እርሱ ግን የእናንተን አካል እና አካሌን በመውሰድ፡ ራሱን በሰዎች ስጋ ዘንድ አስገኝቷል፡ ስጦታዎችን ሰጥቷችኋል፡ ለእኔም ስጦታን ሰጠኝ፡

በእነዚህም ስጦታዎች ራሱን ያሳውቃል። ይህ ምስጢራዊው ምግብ ነው። ምንም ያህል እሱ እራሱን በእኔ እንዲታወቅ ቢያደርግም፡ ማመን ይጠበቅባችኋል፣ ማለት፡ ለማመንም፡ የእምነት ስጦታ ሊኖራችሁ ያስፈልጋል። ታምናላችሁ? [ጉባኤው ሁሉ “አሜን፡” አለ።—አርታዒ።] አሁንስ በዚያ መንገድ እራሱን ከገለጠ፡ ታምኑታላችሁን? [“አሜን።”] በሙሉ ልብ ታምኑታላችሁ? በሙሉ ልብህ ታምነዋለህ? ኦህ፣ እንዴት ድንቅ ነው፡ የሚለኛን ለመስማት ልጠብቀው፡ እሱን እየጠበቅኩ ነው።

169 አንድ ሰው እዚህ ቆሟል። እኔ እንደሚገባኝ፡ በህይወቴ አይቼው አላውቅም። ጥሩ፣ ጠንካራ፣ ጤናማ ሰው ይመስላል፣ እንደዛም ሳይሆን አይቀርም፣ ብቻ—እኔ—አላውቅም። ብቻ ይህ ሰው ቆሟል። አሁን፡ ቀርቤ እጄን ጭኜ ልጸልይለት እችላለሁ፡ ታምናለህን ብዬ ልጠይቀው እችላለሁ። እሱም መጥቶ እንዲህ ሊለኝ ይችላል፦ “ለ—ለ—**እከሌ-እና-እከሌ** እንድትጸልይለት እፈልጋለሁ። እኔ የእግር—ውልቃት አለብኝ። የማያቋርጥ፡ ራስ ምታት አለብኝ። ጨጓራዬ ውስጥ አልሰሮች አሉብኝ፡” ወዘተ ተረፈ። ከሱ—ከሱ፡ እኔ አላውቅም። እነዚህ ነገሮችን ሁሉ ሊል ይችላል።

170 እኔም እለዋለሁ፦ “እሺ፡ ጌታዬ፡ ወንድሜ። እጄን ጭኜ እጸልይልሃለሁ።” ያ ፍጹም ትክክል ነው። በዘመናት ሁሉ ያደረግነው ያ ነውና። ልክ ነው?

171 ነገር ግን፡ አስታውሱ፡ ኢየሱስ የሚመጣበት ዘመን ልክ በሰዶም እንደነበረው፡ በመምጣቱ ጊዜ የተለየ እንደሚሆን ተናግሯል። ያኔ የመጣውም ሰው ጀርባውን ሣራ ወዳለችበት ድንኳን አዙሮ፡ (ከእንግዲህ “አብራም” አትባልም) “አብርሃም፡” እንጂ አለው።

172 አያችሁ፡ ከአንድ ቀን በፊት፡ አብራም ይባል ነበር። ራእይ አይቶ ነበርና፡ ጌታም “ስምህን እቀይራለሁ፡” ብሎት ነበር።

173 እዚጋር ደግሞ፡ ጌታ ራሱ፡ በሰው አምሳል ተገልጦ መጣ፡ ከእርሱ ጋር በላ ጠጣ። አለውም፦ “አብራሃም፡ ሚስትህ ሳራ፡ ወዴት አለች? ” ኤስ-ኤ-አር-አር-ኤ፡ ሳይሆን ኤስ-ኤ-አር—አር-ኤ-ኤች።

እርሱም “በድንኳኑ ውስጥ ከኋላህ ናት፡” አለው።

174 “ከሃያ-አምስት ዓመታት በፊት በገባሁት ቃል መሠረት፡ ልጎበኛችሁ ነው፡” አለው።

175 ሳራም ለእራሷ ሳቀች። ወድያውኑ፦ “ሳራ በድንኳን ውስጥ ሆና፡ ‘ይህ እንዴት ይሆናል? ብላ ሳቀች” አለው፡ ኧህ-ህ። “ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን? ” አያችሁ? ምንም የለም። የስ፡ ስር።

176 ተስፋ ቃል የገባለት፡ ቃል የሆነው ኢየሱስ፡ “እርሱ፡ የሰው ልጅ፡” ነው፡ (ይሄን ታምናላችሁ? ) “እናም ዓለም እንደ ሰዶምና ገሞራ በሚሆንበት በመጨረሻው ቀን ይመጣል ራሱንም ይገልጣል።” ይሄን ታምናላችሁ አይደል?

177 አንድ ጸሎት ከማድረጋችን በፊት፣ ከመካከላችሁ አንዳንዶቻችሁ የሰው ልጅ አሁንም እንደ ትናንትናው፣ ዛሬም፣ ለዘለአለም ያው እንደሆነ ለማየት ጸልዩ። አሁንም እንዲሁ ከሆነ መርምሩት፡ እንዲህ በሉት፦ “ጌታ ሆይ፡ ሰውዬው

እኔን አያውቀኝም፡ አንተ ግን ትናንትናና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው እንደሆንክ አውቃለሁ በሉት፡" እንደነገራችሁ ከሆነ መርምሩ።

የስ፡ ስር። አሁን ለአፍታ ያህል ጭንቅላታችሁን ቀና አድርጉ።

178 ከኋላዬ ነው። ህጻን ልጅ ነው። በትኩሳት አሁን እየነደደ ነው። ህጻን ልጅ ነች። ከዚህ ከተማ አይደላችሁም። ህጻኗ የሆድ ችግር አለባት። አዎን። በቃ እመኑ።

179 አሁን፡ አደርጋለሁ ብሎ እንደተናገረው እንዲሁ ነው? ይህ ሰው በህይወቴ ዘመን አይቼው አላውቅም። የሰማይ አምላክ ይህን ያውቃል።

180 እዚህ ያለው ሰውዬ፡ ጠንካራ እና ጤናማ ይመስላል። ነገር ግን በላዩ ያንዣበበውን ጥላ አይታችሁታል? ይህ ማለት፡ እግዚ አብሄር ካልረዳው በቀር፡ ብዙ ዕድሜ የለውም። ካንሰር አለበት። ሳንባው ውስጥ ነው።

አሁን፡ የሰው ልጅ በዚህ አለ።

በልቡ ውስጥ ስለ አንድ ህጻን ልጅ፡ ስለ አንድ ጨቅላ ልጅ ሸክም አለው። ልክ ነው? እግዚአብሔር ያ ልጅ ምን ችግር እንዳለበት ሊነግረኝ እንደሚችል ታምናለህ? [ያ ወንድም "እንደሚችል አውቃለሁ፡" አለ።—አርታዒ።] ይችላል። የሚጥል በሽታ ዓይነት ትንሽ የሚርት ምልክቶች አሉት። በቅርብ አንዴ ገጥሞታል። ["ዛሬ ጥዋት ነው።"] ልክ ነው፡ ዛሬ ጥዋት። አንተስ ይሄን ልጅ ለማሳደግ በህይወት እንደምትኖር፣ እና ደህና እንደሚሆን ታምናለህ?

181 ቻርሊ ኮክስ የት አለ? የት ነው ያለው? ቻርሊ፡ የት ነህ? ዛሬ ማታ እዚህ ያለ መሰሎኝ ነበር። ቻርሊ፡ እዛጋ። ጌሪ፡ የት ነህ? ላሪስ፡ እዚህ ነው? የሱ ልጅም እንዲሁ፡ ተመሳሳይ ነገር አንድ አይነት ነገር ገጥሞት ነበር። ላሪ፡ የት ነህ ያለኸው? አንዴ ወደዚህ ና። እሺ፡ ይኸውና። እዚህ የሚታያችሁ ልጅ ተመሳሳይ ችግር ነበረበት። አባቱ እና እናቱ በጣም ጥሩ ጓደኞቼ ናቸው። ከብዙ ዓመታት በፊት እዛ ነበርኩና፡ ይህ ህጻን ልጅ የሆነ ነገር ይጀምረዋል፡ ይዘረራል ከዛ ራሱን አያውቅም። የሚጥል በሽታ ነበር። ልጁን ያዝኩትና፡ እግዚአብሄር እንዲፈውሰው ጠየቅኩ። ከዛ ቀን በኋላ አንድም ቀን አልጣለውም። ያ አባቱ ነው፡ እናቱ አንድ ቦታ ቁጭ ብላለች፡ ያውና ትንሹ ልጅ፡ ይሄው ራሱ ነው።

182 ጌታዬ፡ አሁን ያምናሉን? (አመሰግናለው ላሪ።) ያምናሉ፡ ጌታዬ? የሰማይ አምላክ ያንኑ ነገር ይሰጥህ አንተም ልጁን ለማሳደግ ኑር። እግዚያብሔር ይባርክህ።

እንጸልይ።

183 አምላኬ ሆይ እርዳው። ምህረትህ ጸጋህ በእርሱ ላይ እንዲሆንና እንዲባርከው እጸልያለሁ። በኢየሱስ ስም።

184 አሁን ወደ ሉዊዚያና፡ በደስታ ተመለስ፡ እግዚአብሔርን ስለ እርሱ አመስግኑ።

185 ኦህ፡ አዎን፡ ከሉዊዝያና ነው፡ በትክክል፡ ከቻርልስ ሐይቅ ዙርያ ነው። ትክክል። እየሽ፡ አሁን የምታስቢውን ሐሳብ መረዳት እችላለሁ። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!

186 አዎን፡ መልካም ምኞት—እየተመኘሽ ነሽ፡ ልጅ መውለድ ትፈልጊያለሽ። ልጆች አሉሽ፣ ሁለት ልጆች፣ ተጨማሪ እየፈለግሽ ነው። የኔ እህት፡ የሰማይ አምላክ ይሰጥሽ። ነይ ወዲህ ቅረቢ፡ እጆቼን ልጫንብሽ።

187 አምላክ ሆይ፡ ተገቢ ምክንያት ነውና፡ ለዚህች ሴት የልቧን መሻት ስጣት። በኢየሱስ ስም። ኣሜን።

አሁን ሂጂ ልጅሽን ተቀበዪ።

188 እግዚአብሔር መልካም አምላክ ነው። ይህን ታምናለህ? እሱ የሚያስፈልገንን ሁሉ ያውቃል። ካመንን ፍላጎታችንን ሁሉ ያቀርብልናል። "ብታምን!" ብሏልና፤

189 እጅህ ጭብጬ ሰላም ብዬሃለሁ። የት እንደነበረ አሁን አላስታውሰም እንጂ፡ እጅህን ጨብጨዋለሁ። በትክክል አላስታውሰም፡ አንድ ቦታ ግን አብረን ነበርን፡ ዛሬ የሆነ ቦታ ነበርን፡ የት እንደነበረ ግን አላውቅም። አሁን መነጋገር የፈለግነው ግን፡ እሱ አይደለም። ስለ ሌላ ሰው እንድጸልይ ፈልገህ፡ ስለ ሌላ ሰው ለመነጋገር ወይም ለመጸለይ እዚህ ድረስ መጥተሃል። በትክክል። እሱ እዚህ የለም። በጆርጂያ ውስጥ ነው፡ ታሟል። በአካል መታመም፡ ብቻ አይደለም፡ በመንፈስ ታሟል፡ የአጎትህ ልጅ ነው። ለእሱ ስለቆምክ እግዚአብሔር ይህን እንደሚያደርግልህ ታምናለህ? አምነሃል? ወደዚህ ና አብረን እንጸልይ።

190 አምላክ ሆይ፡ ሄዶ ይህን ወደ እግዚአብሔር የሚጮኸውን ሰው ያገኝ ዘንድ፡ ለዚህ ሰው የልቡን መሻት ሰጠው። በኢየሱስ ሰም እጠይቃለሁ። ኣሜን።

እግዚያብሔር ይባርክህ፡ አትጠራጠር። በሙሉ ልብህ እመን።

191 እንዴት ነህ? እጅህን መድረስ ስላልቻልኩ አይደለም እጅህን ያልጨበጥኩት፡ አንቺ እጅሽን ስትዘረጊ፡ እኔ ሌላ ነገር እያየሁ ነበር። ጥቁር ጥላ ነው፡ ትክክለኛ ጨለማ። ምክንያቱ ይህ ነው። እጅህን እንደያዝኩ አውቃለሁ፣ በዚያ መንገድ መለየት እችል ነበር፡ አየህ። ግን ካንሰር ነው። እግዚአብሔር ሊያሰወግደው እንደሚችል ታምናለህ? ጡትህ ላይ ነው፡ በግራ በኩል። ወደ ካሮላይና ተመልሰህ ጌታ ስለፈወሰህ ማመስገን ትፈልጋለህ፡ አይደል? ምን ለማለት እንደፈለግኩ ገባህ? አብረን እንጸልይ።

192 አምላክ ሆይ፡ አሁን ህያው በሆነው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ልጆች የእግዚአብሔርን እንጀራ እንደሚበሉ፡ ይህም ልጅ ይህን እምነት ይባረክበት፡ እርሱም ስለፈውስ እግዚአብሄር የሚሰጠው እንጀራ ነውና። ሄዶ ደህና ይሁን፡ በኢየሱስ ሰም። ኣሜን።

እግዚአብሔር ይባርክህ ወንድሜ። በሙሉ ልብህ እመን።

እንዴት ነህ?

193 ይህ አሰደሳች ጊዜ ነው? በህዝቡ ላይ አድናቆት የወረደ ይመስላል። ወይም፣ ምናልባት፣ ጆሮዎቼ፣ ልክ የሆነ ነገር "ፊው!" እንደሚል ተሰምቶኛል፤ ልክ እንደ፡ "ፊው፡" እንደሚል፡ ድምጽ ተሰምቶኛል፡ አያችሁ። የልጆች እንጀራ ነው። አያችሁ? የእናንተ ነው። ለእናንተ ነው። ለእኔ አይደለም፤ ለእናንተ እንጂ። እኔ አሁን በዚህ ሰዓት፡ እጅግ ደስተኛ ነኝ፡ ምንም… እኔ እስከማውቀው ድረስ፡

መልካም ነው፤ በሚያስፈልገኝ ጊዜ ግን፡ ለእኔም እንጀራ ነው። ለእናንተም እንጀራችሁ ነው። ማበረታቻ ነው። ለአንተ ህመም አይደለምና፡ ልባችን ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ያበረታልናል።

194 አደርጋለሁ ያለውን ነገር፡ ጊዜው አሁን ነው፡ “በሰዶም ዘመን እንደ ሆነ፡ የሰው ልጅ በሚገለጥበት ጊዜ፡ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናል።” አያችሁ? “እነሆ፡ ከታላቁና ከሚያስፈራው ከእግዚአብሔር ቀን በፊት ነቢዩን ኤልያስን እልክላችኋለሁ። የህዝቡን ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል።” አያችሁ? አያችሁ?

195 “የዚያን ጊዜም ጻድቃን—በክፉዎች አመድ ላይ ይራመዳሉ፡ ይዘላሉ።” እንደ ምድጃ ይቃጠላሉ፡ አያችሁ፡ ምድር ትነዳለች። ወደዚያ እንደሚወድቅ እናያለን። እሳተ ገሞራም በምድር ላይ ይሰፋፋል፣ ሰማያትም ይቃጠላሉ።

የዘመናት አለት ሆይ፣ አሁን እና ያኔም ማረኝ።

196 እንዴት ነሽ? እንግዲህ ያንቺ፡ አንድ ነገር ነው፡ የእመቤቶች ችግር፡ የሴት ችግር አለብሽ። ሌሎች ነገሮችም አሉብሽ። ትጨነቂያለሽ፡ የምትጨነቂበት ዕድሜ ላይ ደርሰሻል። ብዙ አይነት ውስብስቦች አሉብሽ። በዚህ ሁሉ ግን፡ አንድ መሻት አለሽ፡ መንፈስ ቅዱስ መሞላት። አዎን። እውነቱ ይህ ነው። እንዲሁ እንደሆንሽ ታምኚአለሽ... ንስሓ ገብተሻል በደንብ? እጄን በአንቺ ላይ ጭኜ እግዚአብሔር እንዲሠጥሽ ከጠየቅሁት፣ መንፈስ ቅዱስ እንደሚመጣ ታምኚአለሽ? [ያቺ እህት “አዎን፡” አለች።—አርታዒ።] ይሄን ታምኚአለሽን? [“የሰ፡ ሰር።”] እንጸልይ።

197 አምላክ ሆይ፡ በሐዋርያዊ መልክ እጄን በዚህች ሴት ላይ እጭናለሁ፡ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት እንድትቀበል እጠይቃለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ትቀበለው። ኣሜን።

198 አትጠራጠሪ። የአንቺ ነውና፡ አየሽ። ለአንቺ ነው። የ—የልጆች እንጀራ ነውና።

199 “የሴቶች ችግር፡” ነው ባልኩሽ ጊዜ ደንገጥ ብለሻል፡ አይደለም'ዴ? ምክንያቱ የነበረብሽ ነገር እሱ ስለሆነ፡ ነው። አሁን፡ ከአሁን በኋላ እንደምትፈወሺ አምነሻል አይደል? ጌታን እያመሰገንሽ፡ ሂጂ።

200 እንዴት ነህ? በሙሉ ልብህ ታምናለህ? ከረጅም ጊዜ በፊት እንደነበረው መብላት እንደምትችል ታምናለህ? እሺ። ሂድና፡ “ጌታ ሆይ፡ ተመስገን። አምናለሁ፡” በል። የጌታ ህልውና።

201 የጀርባ ችግር እንደሚተውህ እና ደህና እንደምትሆን ታምናለህ? እሺ። በል እንግዲህ፡ እግዚአብሔር ያደርግልሃልና፡ “አምላክ ሆይ፡ ተመስገን፡” እያልክ ሂድ።

202 ደህና እንደምትሆን፣ ጌታ እንደሚፈውስህ፣ እና የአርትራይተስ በሽታ ለቆህ እንደሚሄድ፣ ደህና እና ጤናማ እንድምትሆን ታምናለህ? ታምነዋለህን? በል እያመሰገንከው፡ “ጌታ ሆይ፡ በሙሉ ልቤ ተቀብያለሁ፡ አምኛለሁ፡” እያልከው፡ ሂድ።

ሁላችሁም ስለ እሱ ምን ታምናላችሁ?

203 አንተ እዚያ ያለኸው፣ ከጎንህ በተቀመጠችው ሴት ላይ እጅህን ጫን፣ የቫሪኮስ ቨይን እና የአርትራይተስ በሽታዎች ይተውሻል ብለህ ንገራት። እሷ... ? ...

204 እግዚያብሔር ይባርክሽ። አሁን ደህና እንደምትሆኚ ታምኚአለሽ? ወደ ቤት ሂጂ ተከናወኚ። እግዚያብሔር ይባርክሽ። መንገድሽ ሂጂና፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ አመሰግንሃለሁ፡" በዪው።

205 እንዴት ነሽ? የሴቶች ችግር፡ ከአንቺም ለቆ እንደሚሄድ፡ እና ደህና እንደምትሆኚ ታምኚአለሽ? "ጌታ ሆይ፡ አመሰግንሃለሁ፡" እያልሽ፡ ሂጂ።

206 እንዴት ነሽ? ["ቻርቲሌጅ ተንሸራትቶብኛል፡" አለች እህት።—አርታዒ] ውይ፡ ምነው፡ ምነው! ["ቶተን።"] ስምሽን አውቀዋለሁ። ["ቶተን።"] ድሮ በባፕቲስት ቤተ ክርስትያን ፓስተር በነበርኩ ጊዜ—አውቅሻለሁ... ["ቶተን።"] ቶተን። ["ዴላ ቶተን።"] እህት ዴላ ቶተን። አሁን በጀርባ ህመም ኣየተሰቃየሽ ነሽ። ["አዎን።"] ከዛሬ በኋላ ግን፡ ደህና ትሆኚአለሽ። እንደሚፈውስሽ ታምኚአለሽ? ከአመታት በፊት በሚሊታውን ባፕቲስት ቤተክርስቲያን የተፈጠረውን ታስታውሻለሽ አይደል? ["እዎ አስታውሳለሁ!"] ዛሬም ያው አምላክ ነው። እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እህቴ።

ጆርጅ ራይት፡ የት ነህ? ታስታውሳለህ? አቤት፡ ይገርማል...

አምነሻል፡ በዚህ ቅባት፡ እጆቼን በአንቺ ላይ ብጭን፡ እንደምትድኚ ታምኚአለሽ? ነይ ወደዚህ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ትፈወሰ። ኣሜን። እምነት ይኑርሽ!

እሺ፡ ሁላችሁ በሙሉ ልባችሁ ታምናላችሁ?

207 ይህች እመቤት ሰናያት፡ የድሮውን ትዝታ፡ ያስታውሰናል! በርግጥ፡ ስሟ ትዝ አይለኝም፡ ግን... [አንድ ሰው "ቶተን፡" ነው አለ።—አርታዒ።] ቶተን። ቶተን፡ ልክ ነው። ኧረ፡ አዎ፡ ልጇ በርቲ ነበረች። ትክክል ነው። በትክክል ትክክል ነው። ከራሴ በላይ የሆንኩ እንዳይመስላችሁ፣ እንደምታውቁት፡ በመጠኑ ቢሆንም እኔ... ልገልጸው አልችልም።

208 ብቻ እመቤት፡ የጀርባ ህመምሽ አሁን የለም። ሂጂና፡ ጌታ አመስግኚ፡ "ጌታ ሆይ፡ አመሰግናለሁ፡" በዪ።

209 ልብ ህመም እንደሚተውህ፡ እና እንደምትድን ታምናለህ? በል፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ተመስገን፡" እያልክ፡ በደስታ ሂድ፡ እመን። እሺ። አሁን እመኑ። አትጠራጠሩ።

210 ነይ፡ እመቤት። በሙሉ ልብሽ ታምኚአለሽ? ብዙ ችግሮች አሉብሽ። የጀርባ ህመምም፡ አለብሽ። ጌታ እንደሚፈውስሽ ታምኚአለሽ? እሺ፡ በደስታ፡ ሂጂ። እሱ ነው፡ እንዲህ እንዲሰማሽ የሚያደርግሽ ራሱ ነው። ጌታን አመስግኚ። እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እህቴ።

211 እንዴት ነህ፡ ወዳጄ። አምላክ የዚያን ሕፃን መረበሽ ፈውሶ እንደሚያድን ታምናለህ? ታምናለህ? እሺ። ሰላም ነው፡ ጓደኛዬ፡ እጅህን ልጨብጥህ።

212 አምላክ ሆይ፡ ያን ክፉ ነገር ከዚህ ህጻን ላይ አስወግድ፡ ጤናማ ህይወት ይኑር። በኢየሱስ ስም። ኣሜን።

213 እግዚአብሔር ይባርክህ ወንድሜ። ያንን ታምናለህ አይደል? ደህና ትሆናለህ። በፍጹም አትጠራጠር።

214 ለልብ ህመም ገና ወጣት ነህ። እግዚአብሔር እንደሚያድንህ ታምናለህ? “ጌታ ሆይ፡ ስለፈወስከኝ፡ አመሰግንሀለሁ፡” እያልከው፡ ሂድ።

215 እግዚአብሔር የሆድ ችግርን እንደሚፈውስ እና እንደሚያድንህ ታምናለህ? ሂድ፡ ደስ ይበልህ፡ “ጌታ ሆይ፡ አመሰግንሃለሁ፡” በለው።

216 አሁንም አምላክ ነው፡ አይደል? ማድረግ ያለብህ ብቸኛው ነገር ማመን ብቻ ነው. ትክክል አይደለም? የመጨረሻው ዘመን የሰው ልጅ ታምነዋለህን?

217 እዚህ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የሆነ ነገር ተከስቷል፡ እንጃ... የት እንዳለ ለማግኘት በመሞከር ላይ ነኝ። አንድ ሰው እምኖ የሆነ ነገር አድርጓል። ወይም፡ በሚቀጥለው እሁድ፡ ወይም በቻልኩ ቀን አገኘዋለሁ። አንቺ—ነሽ... ያቻት እንደገና። እጅሽን አውጥተሻል። እግዚአብሔር ያንን የልብ ችግር እንደሚፈውስ፡ ጤነኛ እንደሚያደርግሽ፣ ሴት ልጅሽንም እንደሚፈውስ—ታምኚአለሽ... አምነሻል? ወይዘሮ- ኔፍ፡ እግዚ አብሔርን ታምኛለሽ... ሊዮ ኔፍ። እኔ አላውቅሽም፡ ነገር ግን ነሽ። የልብ ህመም አለብሽ፣ እና ታናሽ ሴት ልጅሽም የኩላሊት ህመም ገጥሟታል። ደህና እንደምትሆን ታምኛለሽ? እምነትሽ አድኖሻል። በሙሉ ልብሽ እመኚ።

218 ከኋላ ገንዳው አጠገብ ያለኸው፡ ከሆድ ህመምህ ጋር ከኋላ ቆመሃል፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ፈውሶሃል።

219 ትናንትናና፣ ዛሬ፣ ለዘላለምም ያው እንደሆነ። ታምናለህ? አሁን እጆቻችንን እርስ በእርሳችን እንጫን። ኦህ፡ ያለንበትን ሰዓት አስቡ፡ ዘመኑን አስቡ። የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ መገኘት ውስጥ እንዳለን አስቡ። በመጨረሻው ቀን ይህን እንደሚያደርግ ቃል ገብቷል። እኔም በእነዚህ መሃረቦች ላይ እጆቼን እጭናለሁ።

220 አምላክ ሆይ፡ እነዚህን የሚነኩ አካሎች ፈውስ እንዲያገኙ መሃረቦቹን እንድትባርክ እጸልያለሁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም።

221 አሁን፡ እርስ በርሳችሁ እጆቻችሁ እንደጫናችሁ፡ እያንዳንዳችሁ የክርስቶስ አካል ብልቶች ናችሁ። የልብን ምስጢር ሊገልጥ እና እነዚህንም ነገሮች እንደሚያደርግ ቃል የገባው መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ውስጥም አለ። እናንተ የእርሱ አካል ናችሁ፣ እርሱም የእናንተ አካል ነው። እንግዲህ፡ “ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፡” ብሏል። እናንተን ነው። “እጃቸውን በሕሙማን ላይ ቢጭኑ፡ ይድናሉ።” አሁን፡ እጅ ለጫናችሁበት ሰው ጸልዩለት እንጂ፡ ለራሳችሁ አትጸልዩ፡ ምክንያቱ እነሱም ለእናንተ ይጸልያሉ። አሁን አብረን እንጸልይ፣ እና በዚህ ሕንፃ ውስጥ ታማሚ ሰው አይኑር። ውድ ወንድሞቼ፡ እና እህቶቼ፡ ለምን እንዘገያለን፡ የተናገርንለት ዋናው ነገር፡ ይኸው፡ እግዚአብሔር፡ ራሱም መንፈስ ቅዱስ፡ እዚሁ ይኸው።

222 የተወደድክ ኢየሱስ ሆይ፡ ስለ መገኘትህ እውቅና እየሰጠን ነን። በቀደም ለት፡ ያንን ሕፃን ከሞተ በኋላ፡ በእምነት ጸሎት ወደ ሕይወት መልሰህ አመጣኸው። አምላክ ሆይ፡ መድረስ ያልቻልናቸው ብዙ ሰዎች በዚህ አሉ፡ ጊዜው ሄዷል፡ እነሱ ግን እጆቻቸውን አንዱ በሌላው ላይ ጭነዋል። አማኞች

ናቸው። ከሙታን በተነሣው፡ ትናንትናና ዛሬ ለዘላለምም ያው በሆነው፡ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ፊት፡ ተቀምጠናል።

223 ሰይጣን ሆይ፡ ተሸንፈሃል! ኢየሱስ ክርስቶስ አሸንፎሃል! ከሙታን ተነስቶ ዛሬ ምሽት በመካከላችን ቆሞ፡ ይህንን የመጨረሻውን ቀን መልእክት አረጋግጧል። ህዝቡን ልቀቅ! በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ከሁሉም ውጣ! "በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ" አውጥተንሃል። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ከዚህ ጉባኤ ውጣ!

224 ፈውስ የተቀበላችሁ ሰዎች ሁላችሁ በእግራችሁ ቁሙ። ፈውስ የተቀበለ ሰው ሁሉ በእግር ይቁም። አሁን እጆቻችሁን አንሡ እና አመስግኑት!

"አሁን ፈውሴን ተቀብያለሁ፡" በሉት ለእግዚአብሔር። "አሁን ፈውሴን ተቀብያለሁ። አንተ ትናንትናም፡ ዛሬም፡ ለዘላለምም፡ ያው ነህ ክርስቶስ። አሁን አምንሃለሁ፡ አለማመኔን እርዳው። ኣሜን።"

> ኦ፡ አመሰግነዋለሁ፡ አመሰግነዋለሁ፡
> ስለ ኃጢአተኞች የታረደውን በግ አመሰግናለሁ፡
> ሰዎች ሆይ፡ ሁላችሁ ክብር ስጡት፡
> ደሙ ዝገትን ሁሉ አሰወግዷልና።

225 እሱን አትወዱትምን? [ጉባኤው ሁሉ፡ "አሜን፡" አሉ።—አርታዒ።] እንግዲያውስ እናመስግነው። ወንድማችን ሊያሰናብተን ወደዚህ ሲመጣ፡ ሁላችሁም፡ እጆቻችሁን ወደ ላይ አንስታችሁ፡ ክብርን ስጡት።

**መንፈሳዊ ምግብ በትክክለኛው ጊዜ** AMH65-0718E

(Spiritual Food In Due Season)

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ እሁድ ማታ፡ ሐምሌ 18፡ 1965፡ ጀፈርሰንቪል፡ ኢንዲያና፡ U.S.A. ከሚገኘው ከብራንሃም ተበርናክል፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይስ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግሰ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2023 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org